# ድሬ

19ኛ ዓመት | ቁጥር 854 | ሳምንታዊ ዕትም | ረቡዕ | ህዳር / 26 / 2016 ዓ.ም


# የ18 ኛው የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በአል በድሬዳዋ በድምቀት ተከበረ





"ብዝሐነትና እኩልነት ለሐገራዊ አንድነት" በሚል መሪ ቃል በድሬዳዋ አስተዳደር ሲከበር የነበረው 18ኛው የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በአል በለገሐር አደባባይ በቢል ቦርድ ምርቃት የተጀመረ ሲሆን የማጠቃለያ ፕሮግራሙም በሲምፖዚየምና በተለያዩ ሁነቶች ተካሄዷል።

በሲምፖዚየሙም የተገኙት የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ የተከበሩ አቶ ከድር ጁሀር ፣ የድሬደዋ አስተዳደር ምክር ቤት ም/አፈ ጉባኤ ክብርት ወ/ሮ ከሪማ አሊ፣ የአስተዳደሩ ም/ከንቲባ አቶ ሀርቢ ቡህ፣ የሀረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አፈ ጉባኤ የተከበሩ አቶ ሱልጣን አብዱሰላም፣የሀረሪ ሊግ ም/ሀላፊ የተከበሩ ወ/ሮ ዚነት ዩሱፍ፣ የጨፌ ኦሮሚያ ምክር ቤት ተወካይ የተከበሩ ወ/ሮ አልፍያ፣የሀይማኖት አባቶች ፣ አባ ገዳዎች፣ኡጋዞች፣የሀገር ሽማግሌዎች፣የካቢኔ አባላት፣ ከፍተኛ የድርጅት አመራሮች እንዲሁም የሴክተር መስሪያ ቤት ሀላፊዎችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተውበታል።

የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ የተከበሩ አቶ ከድር ጁሀር የመክፈቻ ንግግር ያደረጉ ሲሆን በንግግራቸውም የፌዴሬሽን ምክር ቤት የፀደቀበት ህዳር 29 የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በአል ተብሎ በሚያዚያ 21/1998 ዓ.ም መወሰኑ በአሉ በሕብረ ብሔራዊ አንድነት እንዲዳብርና በጋራ የመበልፀግ ህልማችንን እውን ለማድረግ ትልቅ ሚና ስላለው 18ኛውን የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በአል ስናከብር ህብረ ብሄራዊ አንድነታችን በፅኑ መሰረት ላይ ለማቆም በምናደርገው ሁለንተናዊ ጥረት ለሀገራችን ኢትዮጵያ የቅንጦት ጉዳይ ሳይሆን ሀገርን አንድ አድርጎ ሰላሟንና ሉአላዊነቷን አስጠብቆ የማስቀጠል የህልውና ጉዳይ መሆኑን አውቀን ሁላችንም የሚጠበቅብንን የዜግነት ሀላፊነት ለመወጣት ከመቼውም ጊዜ በላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅብናል ብለዋል።

የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት ም/አፈ ጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ከሪማ አሊ 18ኛው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በአል በድሬዳዋ አስተዳደር "ብዝሐነትና እኩልነት ለሐገራዊ አንድነት" በሚል መሪ ቃል በተለያዩ ሁነቶች በማክበርና በመንግስት ተቋማቶች ፤ በወጣቶችና ሴቶች መድረክ እንዲሁም በህዝብ ለህዝብ መድረኮች በፌዴራሊዝም ስርአት ላይ በቂ ግንዛቤ ለመፍጠር የመመያያ ሰነድ ቀርቦ ውይይት ሲካሄድ መቆየቱን ጠቅሰው፤ ይህ በአል አንድነታችንን በማጠናከር ረገድ ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ በመሆኑ ይህንን ታሳቢ በማድረግ በአሉን ከማክበር ባሻገር በምናደርገው የብልፅግና ጉዞ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን ለማስቀም ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪ ቀረበ




የድሬዳዋ አስተዳደር ሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ወ/ሮ ሁክሚያ መሀመድ 32ኛው አለም አቀፍ የነጭ ሪባን ቀንን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን ለማስቆም ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡

በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለማስቆም የሚደረገው 16ቱ ቀናት የጸረ-ጾታዊ ጥቃት ዘመቻ / የነጭ ሪቫን ሳምንታት ከህዳር 16 እስከ ታህሳስ 01 በተለያየ መልኩ በመላው አለም የሚከበር ሲሆን በዘንድሮ 2016 ዓ.ም በአለም አቀፍ ደረጃ ለ32ኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ለ18ኛ ጊዜ "መቼም፣ የትም፣ በምንም ሁኔታ ፆታዊ ጥቃትን ዝም አንበል" በሚል መሪ ቃል እንደሚከበርም ገልጸዋል።

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# የአለም አቀፍ የኤች አይ ቪ ኤድስ ቀን በድሬዳዋ በፓናል ውይይት ተከብሮ ዋለ




በሔለን ሽጉጤ

"በላቀ የማህበረሰብ ተሳትፎ ኤች አይ ቪን እንግታ" በሚል መሪ ሀሳብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ36ኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ለ35ኛ ጊዜ በአስተዳደሩ በተለያዩ መርሃ-ግብሮች ተከበረ።

ባሳለፍነው ሳምንት በድሬዳዋ ጤና ቢሮ አዘጋጅነት የአለም የኤች አይ ቪ ኤድስ ቀን ላይ የአስተዳደሩ አመራሮች፣ የሀይማኖት አባቶች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ተወካዮች፤ የጤና ጣቢያ ኃላፊዎችና የጤና ባለሞያዎች፤ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚሠሩ ማህበራት፣ ባለድርሻና ጉዳዩ የሚመለከታቸው እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት የፓናል ውይይት ተካሂዷል።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የድሬዳዋ አስተዳደር ኤሌክትሪክ ሀይል አገልግሎት የማዕከል እድሳት ተጠናቆ በይፋ ተመረቀ



የድሬዳዋ አስተዳደር ኤሌክትሪክ ሀይል አገልግሎት ለደንበኞቹ እና ለሰራተኛው ምቹ የስራ ቦታን እና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ያስችል ዘንድ ማዕከሉን ዘመናዊ በሆነ መልኩ አድሶ በማጠናቀቅ በአስተዳደሩ ከንቲባ ክቡር ከድር ጁሀር በይፋ ተመርቋል፡፡

የማዕከሉ እድሳት 18,957,648 የፈጀ ሲሆን በውስጡ ደረጃቸውን የጠበቁ የኃላፊ ቢሮዎች፣ከ50 በላይ ሰራተኞችን መያዝ የሚችሉ አገልግሎት መስጫ ቢሮዎች፣ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ፣የህክምና መስጫ፣ የህጻናት ማቆያ እንዲሁም 22 ሺ ሰው ማስተናገድ የሚችል ማእከል ሲሆን በአጠቃላይ ለአገልግሎት አሰጣጡ አስፈላጊ የተባሉ መሰረተ-ልማቶች ተሟልተውለታል፡፡

ፕሮጀክቱን በይፋ የመረቁት የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ክቡር ከድር

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ህገ - ወጥ የኮንስትራክሽን ግብዓት አቀማመጥና የግንባታ የተረፈ ምርት አወጋገድን ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ ተዘጋጀ



በሔለን ሽጉጤ

የድሬዳዋ አስተዳደር ግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተዘጋጁ ሁለት ሰነዶች ላይ ለተቋሙ ፈፃሚ አካላት ስልጠና ሰጠ፡፡

የስልጠና መድረኩን የከፈቱት የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ህንፃ ሹም ዋና ዳይሬክተር አቶ ኤፍሬም ግርማይ እንዳሉት ተቋሙ በአስተዳደሩ እየተደረገለት ካለው መጠነ ሰፊ እገዛ የተነሳ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅሙን የሚገነቡ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ የሚገኝ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በዚህም ከሚከናወኑና እየተከናወኑ ካሉ በርካታ ተግባሮች አንዱ በአስተዳደሩ ተጨባጭ ሁኔታ ተቋሙ ከተቋቋመበት ወቅት ጀምሮ የአገልግሎት

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

የአስተዳደራችን መስታወት፤ የህብረተሰባችን አንደበት

# በፈረንሳይና በዴንማርክ አንባሳደሮች የተመራው ልኡካን ቡድን በአዳዳ ገጠር ቀበሌና ሳቢያን አካባቢ ጉብኝት አካሄደ




ባሳለፍነው ሳምንት በፈረንሳይና ዴንማርክ አንባሳደሮች የተመራ ልኡካን ቡድን በአስተዳደሩ የሚስተዋለውን የውሃ ችግር የሚቀርፍ ጥናት ለማጥናት ድሬዳዋ ከተማ የገባ ሲሆን ቡድኑ የፕሮጀክት ማስጀመሪያ መርሀ-ግብሩንም አከናውኗል። በዚህም የት አካባቢ ጥናት ይደረጋል የሚለውን ለመለየት በአዳዳ ገጠር ቀበሌና በሳቢያን አካባቢ ጉብኝት አካሂዷል።

የፕሮጀክቱ ጅማሮ ማብሰሪያ መድረክ ላይም የድሬዳዋ አስተዳደር ክቡር ከንቲባ ከድር ጁሀር ለእንግዶቹ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

በአስተዳደሩ ያለውን የውሃ ችግር ለመቅረፍና የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በጋራ ለመስራት እንዲሁም ልምዳቸውን ለማጋራት ፍቃደኛ በመሆናቸው የፈረንሳይና የዴንማርክ አንባሳደሮችን አመስግነዋል።

ክቡር ከንቲባው በዚህ ስራም የድሬዳዋ አስተዳደር በርካታ ጥቅሞችን እንደሚያገኝ ጠቅሰው በቀጣይ አብሮ መስራቱ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሲሉ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

የድሬዳዋ አስተዳደር የግብርና፣ ውሃ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ሀላፊ አቶ ኑረዲን አብደላ በበኩላቸው አሁን ላይ በአስተዳደሩ ያሉ ነዋሪዎች የከርሰ ምድር ውሃን ለመጠጥ ጥቅም ላይ እንደሚያውሉ አንስተው፤ መስተዳደሩም ያለውን ውሃ በአግባቡ ለመጠቀም እንዲችል በከርሰ ምድር ውሃ ሀብት ዙሪያ ሰፊ ተሞክሮ ካላቸው ሀገራት ልምድ በመቅሰምና ሀብቱን በመንከባከብ በዘላቂነት ለመጠቀም በዚህ መልኩ በቅርበትና በትብብር መስራት ውጤታማ እንደሚያደርግ ገልፀዋል።

አቶ ኑረዲን የፕሮግራሙን ዋነኛ አላማ ሲገልፁ በአስተዳድሩ ያለውን የከርሰምድር ውሃ ሀብት በምን አይነት መልኩ በአግባቡና በዘላቂነት ለህብረተሰቡ ማዋል ይቻላል በሚለው ዙሪያ ጥናት ማከናወንና ዘላቂ መፍትሄ ማምጣት እንደሆነ ተናግረዋል።

ልኡካን ቡድኑ በመስክ ምልከታው የአዳዳ ገጠር ቀበሌ በመገኘት የተፋሰስ ልማት ስራዎችን የጎበኘ ሲሆን በዚህ ስራም የከርሰ ምድር ውሃን በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ ስራ እንደተሰራ ተገልጿል፡፡ ልኡክ ቡድኑም የተሰራውን ስራ አድንቋል።

ፈረንሳይና ዴንማርክ በከርሰ ምድር ውሃ ላይ በጥናት የተደገፈና የዳበረ መረጃ ያላቸው በመሆኑ ይህንን ልምድ ወደ መስተዳደራችን ማምጣት እንደሚገባም አቶ ኑረዲን ተናግረዋል።

አቶ ኑረዲን አያይዘውም የባለሞያዎችን አቅም በመገንባት የተለያዩ ሶፍትዌሮችን በማልማት በአስተዳደሩ የሚስተዋለውን የውሃ ችግር ለመቅረፍ ሀገራቱ ትልቅ እገዛ እንደሚያደርጉም ጠቁመዋል።

አሁን ላይ ባለው የአየር ንብረት መለዋወጥና በሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት የከርሰ ምድር ውሃ ሀብታችን እየቀነሰ እንደሆነ አቶ ኑረዲን ጠቁመው፤ ይሄንን ለመግታት የከርሰ ምድር ውሃ ሀብት መገኛ ቦታዎችን የመጠበቅ፣ የመንከባከብ እና የማጎልበቻ ቦታዎች በአግባቡ የመጠበቅ ሂደት አስፈላጊ መሆኑንም ኃላፊው ተናግረዋል።

በዚህ ዙሪያ ከሁለቱ ሀገራት ጋር በትብብር ለመስራት በሀገር አቀፍም ደረጃ ከውሃ ሀብት ሚኒስትር ጋር ሰነድ እንደተፈራረሙ አቶ ኑረዲን አንስተው የድሬዳዋ አስተዳደርም በዚህ ተጠቃሚ እንደሚሆን ገልፀዋል።

ድሬዳዋ ላይ በስፋት የጎርፍና የድርቅ አደጋ በተደጋጋሚ እንደሚከሰት የተነሳ ሲሆን በጎርፍ የሚያልፈው ውሃ የተለያዩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን በመስራት መሬት ውስጥ እንዲሰርግ በማድረግ ጎርፉ የሚሄድባቸው አሸዋማ ቦታዎች ላይ ግድቦችን በመስራት ላይ እንደሚገኙም የቢሮው ሀላፊ ጠቁመው፤አሁን ላይ እየተሰሩ ያሉ ግድቦችም ከዚህ ቀደሞቹ ለየት ባለ መልኩ መገንባታቸውን ገልፀዋል። በቀጣይም እንደነዚህ አይነት ግድቦች እንደሚበራከቱም ተናግረዋል።

የድሬዳዋ አስተዳደር የሀገር ውስጥና አለም አቀፍ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ከድር አልይ በበኩላቸው በዚህ ፕሮጀክት በዋናነት ድሬዳዋ ውስጥ ያለውን የውሃ መስመር ወደ ዲጂታል ለመቀየር እንደታሰበ ጠቁመዋል። ድሬዳዋም በዚህ ፕሮጀክት በአስተዳደሩ የሚስተዋለውን የውሃ፣ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮና መሰል ችግሮችን በዘላቂነት ልትፈታ እንደምትችል ተናግረዋል።

**በኤደን ሳሙኤል**

# የድሬዳዋ አስተዳደር መንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ አመራሮች እና ሰራተኞች የፀረ ኤች አይ ቪ ኤድስ ቀንን አከበሩ



የዓለም ኤድስ ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ36ኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ35ኛ ጊዜ በተለያዩ መርሃ-ግብሮች ተከብሯል።

“በላቀ የማህበረሰብ ተሳትፎ ኤች አይ ቪን እንግታ” በሚል መሪ ሀሳብ ታስቦ የዋለውን የፀረ ኤች አይ ቪ ኤድስ ቀንን አስመልክቶ ለመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ አመራሮች እና ሰራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ተካሂዷል ።

የድሬዳዋ አስተዳደር መንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ አቶ ብሩክ ፈለቀ በመድረኩ እንደተናገሩት ቢሮው በጤናው ዘርፍ ካቀዳቸው እቅዶች አንዱ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ ስራዎችን አካታች ባደረገ መልኩ መስራት በመሆኑ በሚፈለገው ልክ ለማህበረሰቡ ግንዛቤ የሚሰጡ መረጃዎችን ባሉን የሚዲያ አውታሮች ተደራሽ ማድረግ አለብን ብለዋል።

የዓለም የኤድስ ቀንን ምክንያት በማድረግ ስለ በሽታው አጠቃላይ ሁኔታና እያስከተለ ያለውን ማህበራዊ የጤና ችግር በማስመልከት እንዲሁም በመከላከያ መንገዶች ላይ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ውይይትም ተደርጓል፡፡

**በሰላም ለማ**

## ማስታወቂያ

**ለአቶ መሀመድ ሁሴን**

**ባሉበት**

አመልካች ወ/ሮ ሚስራ መሀመድ በዚህ ፍ/ቤት ቀርበው በእርሶ ላይ እርሶ የሉም በማለት የፍቺ ክስ የተመሰረተቦት ስለሆነ እርሶ አልያም ይህን የፍቺ ክስ አቤቱታ ተቃዋሚ ካለ ለ08/04/2016 ዓ/ም ለሆነ ቀጠሮ እንዲቀርቡ ፤ባይቀርቡ ግን በሌሉበት ፍ/ቤቱ የፍቺ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ያሳውቃል፡፡

**የፌ/መ/ደ/ሸ/ፍ/ቤት**

# ኤስ ኦ ኤስ ለ8 የአካል ጉዳተኛ ህፃናቶች የቁሳቁስ ድጋፍ አደረገ




በድሬዳዋ አስተዳደር የሚገኘው ኤስ ኦ ኤስ የህፃናት መንደር ፕሮግራም መንግስታዊ ያልሆነ አለም አቀፋዊ የበጎ አድራጎት ድርጅት ሲሆን በሀገራችን ኢትዮጲያ ወላጆቻቸውን በተለያየ ምክንያት ያጡ ህፃናትን አሰባስቦ ከለላ በመስጠት ራሳቸውን ችለው ሀገራቸውን እንዲያገለግሉ የሚሰራ ድርጅት ነው።

ይህ ድርጅት ግምቱ 221 ሺህ ብር የሚሆኑ የአካል ድጋፍ ዊልቸሮችን ለ8 አካል ጉዳተኛ ህፃናቶች እና የመፀዳጃ ወንበሮች ድጋፍ አድርጓል።

ኤስ ኦ ኤስ የህፃናት መንደር በሀገራችን ኢትዮጲያ ከዛሬ 50 አመት በፊት ስራ እንደጀመረና በእነዚህ አመታት ውስጥም በሀገራችን በተለያዩ ከተሞች ትላልቅ ስራዎችን በመስራት ላይ እንደሚገኝ በኤስ ኦ ኤስ የህፃናት መንደር በኢትዮጲያ የምስራቅ ኢትዮጲያ ፕሮግራም ዳይሬክተር አቶ አንዱአለም ጌታቸው ተናግረው፤ አሁን ላይ በድሬዳዋ አስተዳደር ላይ ኤስ ኦ ኤስ በጀመረው ፕሮጀክትም ለአካል ጉዳተኛ ህፃናት ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ የሚረዳ ዊልቸር እና ለመፀዳጃነት የሚጠቅም ወንበር ድጋፍ መደረጉን ገልፀዋል።

የድሬዳዋ አስተዳደር ሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ እና የማህበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲን በመወከል በርክክቡ የተገኙ ባለሙያዎች ለአካል ጉዳተኛ ህፃናት ይህን አይነት ድጋፍ በመደረጉ አመስግነው ድርጅቱ ለአስተዳደሩ እያደረገ ላለው እገዛ ያላቸውን አክብሮት በመግለፅ ድጋፍ የተደረገላቸው ቤተሰቦች ንብረቶቹን በጥንቃቄ በመያዝ እንዲጠቀሙባቸው መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።.

**በትዕግስት ቶሎሳ**

# ርዕሰ - አንቀጽ

## ፆታዊ ጥቃት_ይቁም !

ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ሁሉንም ሴቶች የሚጎዳ ቢሆንም በተለይም አካል ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንን እና ህፃናትን በይበልጥ ይጎዳል። ይሁን እንጂ ድምፃቸው ሲሰማ እና በቂ ድጋፍ ሲያገኙ አይተዋሉም።

በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት ይቁም! የሚሉ በርካታ ድምፆች ከሰሞኑን ለ16 ቀናት ከአራቱም የአለማችን አቅጣጫዎች ሲሰሙ ሰነባብተዋል፡፡

1. ስለ ፆታዊ ጥቃት ምንነት ፣ጉዳት፣ እንዴት መከላከልና ማስቆም እንደሚቻል ማስተማርና ማሳወቅ፣ ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ተጎጂዎች የህክምና ፣ የምክር ፣ የፍትህ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ተቋማት የትኞቹ እንደሆኑና የት የት እንደሚገኙ በሚዲያ መንገርና ማሳወቅ

2. ስለ ፆታዊ እኩልነትና መገለጫዎቹ፣ ሴቶችን ስለማብቃትና ስለመደገፍ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ፣ በቤተሰብና በማህበረሰብ እድገት ሂደት ውስጥ የሴቶችን እጅግ ወሳኝ ድርሻና ሚናን በሚመለከት በጎና ተምሳሌት የሆኑ ቀጣይ ፕሮግራሞችን ዘገባዎችን በማሰራጨት በተቃራኒው ጎጂ የሆኑትን በመጠቆም በማህበረሰብ አመለካከት ላይ በጎ ተፅዕኖ ማሳደር

3. ፆታዊ ጥቃትና ከዚህ ጋር በተያያዘ ለአድማጭና ተመልካች የሚተላለፉ መልዕክቶች የሚዲያ ዘገባዎችና ፕሮግራሞች ትክክለኛ/በባለሙያ የተረጋገጡ ፣ሚዛናዊና በተገቢ ቋንቋና ቃላት የተዘጋጁ ፣ የተጎጂዎችን ፣የእማኞችን፣ ከጉዳቱ የተረፉትን፣ ደህንነት ፣ መብትና ሚስጥር የጠበቁ ፣ስብዕና እና ስነልቦና የማይጎዱ፣ ማህበራዊ ቀውስ የማያስከትሉና ችግሩን የማያባብሱ መሆናቸውን በማረጋገጥ ተከታታይነት ያላቸው ስርጭቶች አየር ላይ በማዋል የሚዲያውን ዘርፍ ሚና መጫወት

4. ፀረ ፆታዊ ጥቃት እንቅስቃሴ ላይ የተሠማሩ ግለሰቦች ፣ ተቋማት እንዲሁም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር በመተባበር፣ በማስተማርና በማሳወቅ ማህበራዊ ሐላፊነትን መወጣት ከሁሉም ሰው የሚጠበቅ የዜግነት ግዴታ ነው!

# አጀንዳ

## የስርቆት እና ውንብድና ወንጀሎች ምንነትና የህግ ተጠያቂነት

ወንጀል እንደየደረጃው የማህበረሰብን ብሎም የሀገርን ደህንነት አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል እኩይ ድርጊት ነው፡፡ ከየእለት ኑሯችን ጋር በተያያዘ ብንመለከት እንኳ በአብዛኛው ወንጀል በሰዎች አካልና ደህንነት እንዲሁም ንብረት ላይ ሲፈፀም ይስተዋላል፡፡ በንብረት ላይ በስፋት ከሚፈጸሙ ወንጀሎች መካከል ስርቆት፣ ውንብድና እና ዘረፋ ይጠቀሳሉ፡፡ ሆኖም ህብረተሰቡ በእነዚህ ሶስት ወንጀሎች ልዩነት ላይ ያለው መረዳት እምብዛም ነው ማለት ይቻላል፡፡

በዛሬ አጀንዳችን የስርቆትና የውንብድና ወንጀሎችን ምንነት እና የሚስከትሉትን ቅጣት በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

ስርቆት

በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ህግ አንቀፅ 665 መሰረት ስርቆት ማለት ያልተገባ ብልጽግና ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰውን ተንቀሳቃሽ እቃ ወይም ከማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተነጠለን እቃ አንስቶ መውሰድ፣ በቀጥታ የራስ ንብረት ማድረግ ወይም በተዘዋዋሪ ከራስ ንብረት ጋር እንዲቀላቀል ማድረግ ነው፡፡ ይህንን ድርጊት የፈፀመ ሰው የስርቆት ወንጀል በመፈፀም በወንጀል የሚጠየቅ ሲሆን ቅጣቱም እንደነገሩ ሁኔታ ቀላል እስራት ወይም ከአምስት አመት የማይበልጥ ፅኑ እስራት ሊሆን ይችላል፡፡

ወንጀሉን የሚያከብዱ ሁኔታዎች (ከባድ ስርቆት)

ከባድ ስርቆት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 669 ስር የተደነገገ ሲሆን ይህ አንቀጽ በአንቀጽ 665 ስር የተቀመጠውን የስርቆት ወንጀል ማክበጃ ነው፡፡ እንደወንጀሉ ክብደትና በተሰረቀው ዕቃ አይነት፤ የወንጀል አድራጊው የኑሮ ደረጃና ሁኔታ እንዲሁም የአሰራረቅ አይነት ወይም ዘዴን መሰረት በማድረግ የስርቆት ወንጀሉ ከባድ ሊሆን እንደሚችል በአንቀጽ 669 ላይ ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በዚሁ አንቀጽ ላይ ወንጀሉን የሚያከብዱ ምክንያቶች በሶስት ንኡስ አንቀጽ ተዘርዝረው ይገኛሉ፡፡ ይኸውም፡-

በአንቀጽ 669 (1) ስር የተሰረቀው ዕቃ አይነት፡-

- የሀይማኖት ስርአት የሚፈጸምበት ስፍራ ውስጥ የሚገኝ የሀይማኖት ዕቃ፣ በቤተ መዘክር ውስጥ የተቀመጠ ዕቃ፣ ለህዝብ ክፍት በሆነ ህንጻ ውስጥ የተቀመጠ ሳይንሳዊ ኪነ ጥበባዊ ወይም ታሪካዊ ዋጋ ያለው ዕቃ፤

- የተለየ ጠባቂ የሌለው እንስሳ ወይም ሰብል፣ ለቴሌኮሚኒኬሽን፣ ለኤሌክትሪክ ሀይል፣ ለውሀና ፍሳሽ ወይም ለማንኛውም ሌላ ድርጅት አገልግሎት የሚውል ጠባቂ የሌለው መሳሪያ ወይም እቃ ሲሆን

የወንጀል ፈጻሚው ሁኔታ በአንቀጽ 669(2) የስርቆት ወንጀሉን የፈጸመው

- የመከላከያ ሰራዊት አባል ሆኖ ወንጀሉን የፈጸመው በጓደኞቹ ወይም በአለቆቹ ላይ ሲሆን ወይም የተሰረቀው ዕቃ ሰራዊቱን የሚያገለግል ወይም እንዲያገለግል የተመደበ ሲሆን፡

- የመንግስት ሰራተኛ ወይም አንድ የንግድና ይህን የመሳሰለ ልዩ ሥራ የሚያከናውን ሰው የባንክ ሰራተኛ፣ ጠበቃ፣ ውል አዋዋይ፣ የወኪልነት ስልጣን የተሰጠው እንደራሴ ወይም በእንዲህ ያለ ምክንያት የተሰጠውን ስልጣን በማከናወን ላይ የሚገኝ የንግድ ስራ አስኪያጅ ሆኖ ድርጊቱን የፈጸመው በተለይ በተሰጠው ስልጣን ምክንያት በእጁ በገባው የመንግስት፣ የህዝብ ወይም የግል ንብረት ላይ ሲሆን

- ባለሆቴል፣ የቤት አከራይ፣ እቃ አመላላሽ፣ ተሸካሚ ወይም ይህን የመሳሰለ ሥራ የሚያካሂድ ሆኖ የተሰረቀው ንብረት የደንበኛው ሲሆን

- የቤት ሰራተኛ፣ ሰራተኛ ወይም ሥራ ለማጅ ሆኖ ስራውን ምክንያት በማድረግ በአሳዳሪው ወይም በአሰሪው ላይ ጉዳት በሚያደርስ ሁኔታ ሲሆን

ወንጀል ፈጻሚው የአሰራረቁ አይነት

በአንቀጽ 669(3) መሰረት የስርቆት ወንጀሉን የፈጸመው ሰው የአሰራረቁ አይነት ወይም መንገድ

- በሰዎች ወይም በንብረት ላይ ወንጀል ለመፈጸም የተቋቋመ ቡድን አባል ሲሆን

- ስርቆቱን የፈጸመው በተለይ አደገኛ መሆኑን በሚያሳይ በማናቸውም ሌላ ሁኔታ ይልቁንም በማጥቂያ ወይም የመከላከያ የጦር መሳሪያ ወይም የቤት መሰርሰሪያ መሳሪያ በመያዝ ሲሆን ወይም ራሱን የመንግስት ሰራተኛ በማስመሰል ሲሆን ወይም በሌሊት፣ ቅጥር በመጣስ፣ አጥር በመዝለል፣ በር በመስበር ግድግዳ በመሰርሰር፣ ወይም በቡድን በመሆን ሲሆን፡ ወይም ያልተጠበቀ አደገኛ ሁኔታን የህዝብ ብጥብጥን ወይም መቅሰፍትን ይልቁንም እንደግርግር ቃጠሎ፣ ጎርፍ፣ ማዕበል የመሳሰለውን ሽፋን በማድረግ ሲሆን የተፈፀመው ወንጀል ከባድ ስርቆት ይባላል፡፡

በዚህም በአንቀጽ 669 ስር ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ በተገኘ ጊዜ ፈፃሚው በከባድ ስርቆት ወንጀል የሚጠየቅ ሲሆን ቅጣቱም ከአንድ አመት የማያንስ ቀላል እስራት ወይም ከአስራ አምስት አመት የማይበልጥ ጽኑ እስራት ይሆናል፡፡

በልዩ ሁኔታ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 669(1)/ለ/ ስር ከተዘረዘሩት ተግባራት መካከል በቴሌኮሚኒኬሽን እና በኤሌክትሪክ አውታሮች ላይ ስርቆት የተፈጸመ እንደሆነ የቴሌኮሚኒኬሽንንና የኤሌክትሪክ አውታሮችን ለመጠበቅ በወጣው አዋጅ 464/1996 ዓ/ም አንቀጽ 4 መሰረት ቅጣቱ ከአምስት አመት እስከ ሃያ አመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ይሆናል፡፡

ውንብድና

ማንም ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላው ሰው ንብረት የሆነውን ተንቀሳቃሽ እቃ ለመውሰድ እንዲያመቸው ወይም በሚወስድበት ጊዜም ሆነ ከወሰደ በኋላ የገጠመውን ተቃውሞ ለመቀልበስ በሌላ ሰው ላይ የሀይል ድርጊት መፈጸም ወይም ከባድ የሆነ የማንገላታት ተግባር ወይም ከባድ ዛቻ መፈፀም ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ይህን ሰው ለመከላከል እንዳይችል ማድረግ የውንብድና ተግባር እንደሆነ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 670 ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ይህን ወንጀል ፈፅሞ የተገኘ ሰው ከአስራ አምስት አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት የሚቀጣ ይሆናል፡፡

ወንጀሉን የሚያከብዱ ሁኔታዎች (ከባድ ውንብድና)

በወንጀል ህጉ አንቀጽ 671 ላይ የውንብድና ወንጀልን ከባድ የሚያደርጉ ምክንያቶች የተዘረዘሩ ሲሆን ወንጀል ፈጻሚው ወንጀሉን የፈጸመው

- በሰዎች ላይ ወይም በንብረት ላይ የኃይል ተግባር ለመፈጸም በተቋቋመ የወንበዴ ቡድን አባል በመሆን ሲሆን

- ተበዳዩን እገልህለሁ ብሎ እርግጠኛ የሞት አደጋ እንደሚደርስበት በመዛት፣ በጦር መሳሪያ ወይም በተለይ አደገኛ በሆነ ሌላ አይነት መሳሪያ በማስፈራራት ወይም ስቃይ በሚያደርስ ሁኔታ በማንገላታት ወይም ከባድ የአካል ጉዳት በማድረስ ሲሆን

- አደገኝነቱን በሚያሳይ በማናቸውም ሌላ ሁኔታ ሲሆን ወንጀል ፈጻሚው ከአምሰት አመት እስከ ሃያ አምስት አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ሊቀጣ ይችላል፡፡

በሌላ በኩል ወንጀል ፈጻሚው ወንጀሉን የፈጸመው ወንጀል ለመፈጸም ከተደራጀ ቡድን ጋር በመሆን ወይም የጦር መሳሪያ ወይም ሌላ አደገኛ መሳሪያ በመያዝ የህዝብ ጸጥታን አደጋ ላይ የሚጥል ወይም የተለየ ጨካኝነት የሚያሣይ ዘዴን በመጠቀም፣ ወይም የተፈጸመው የሀይል ተግባር ዘላቂ የአካል ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ ሲሆን ቅጣቱ እድሜ ልክ እስራት ሲሆን የውንብድና ወንጀል አፈጻጸሙ እጅግ ከባድ በሆነ ጊዜ የሞት ቅጣት ሊሆን እንደሚችል የወንጀል ህጉ ደንጎት ይገኛል፡፡ የጦር መሳሪያን በመጠቀም በቡድን በመሆን በልማደኝነት የውንብድና ወንጀልን መፈጸም በሞት እንደሚያስቀጣ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 671 በግልጽ ደንግጎት ይገኛል፡፡

የድሬዳዋ አስተዳደር የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ በየሳምንቱ የሚታተም **ሚያዚያ 21/1996 ዓ.ም** ተጀመረ

ረቡዕ - ህዳር / 26 / 2016 ዓ.ም

ድሬ ጋዜጣ

**አዘጋጆች**
በድሉ ኃይሌ
ማቲያስ እንዳለ
እስከንድር ኡስማን

**ፎቶ ግራፈር**
ሰላም አበበ

**ዋና አዘጋጅ**
ሔለን ሽጉጤ
( 09 20 26 49 55 )

**ሌይአውት ዲዛይን**
ሰማን ሙስጠፋ

**የኮምፒዩተር ፅሁፍ**
ዘነቡ ፋንቱ

ስልክ - 025 111 6065
ፋክስ - 025 111 4972 ፖ.ሳ.ቁ 370
ኢ-ሜይል - Info_pubbure@yahoo.com
ዌብሳይት - www.direcomm.gov.et
ፌስቡክ - Dire Dawa Geovernement Communication Affairs Bureau (@DDGCAB)

# ሙስና የጋራ ጠላታችን ነው? /ክፍል - 1

በስንታየሁ እንግዳ

ባሳለፍናቸው ሳምንታት የሀገራችን ነቀርሳ ስለሆነው ስለሙስና «ሙስና የጋራ ጠላታችን ነው እንታገለው» በሚል መሪ ሃሳብ በመንግስት ተቋማት በተለያዩ ሁኔታዎች ሲከበር እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡ በርግጥ ሙስና በዓመት አንዴ በሚደረግ የፓናል ውይይትም ሆነ በሌሎች ፕሮግራሞች በማክበር መፍትሄ የምንሰጠው ጉዳይ ባይሆንም እንደ መንግስት ችግሩን ለመቅረፍ ዓመቱን ሙሉ እንደሚሠራ ይታወቃል፡፡ ቁብ ነገሩ ግን ሙስናን ለመከላከል የሚሠሩ ሥራዎችን ስንቶቻችን ደግፈን ይሆን? ለማንኛውም እኔም ባለችኝ ኢምንት እምነትና ሀገራዊ ተቆርቋሪነት ስለሙስና ከፃፍኩት የመጀመሪያውን ክፍል እነሆኝ፡፡ እንደው ግን በሞቴ ሙስና የጋራ ጠላታችን ነው? ጠላታችን ከሆነስ ስለምን የሆነ ጠላትን እንደሚዋጋ ሰው ስለምን አምርረን አልተዋጋነውም?

ዘመናት በዘመናት ሲተካኩ ህይወትም በህይወት ላይ አንዱን በአንዱ እየተካች ትናንት ዛሬን ወልዶ ዛሬ ደግሞ ነገን ለመውለድ ቀጠሮ ይዞ እኛና ጊዜ አብረን አለን፡፡ በዚህ የጎዞ ሂደት ክፉና ደጉን እያሳለፈ እዚህ የደረሰው ህዝባችን ከቅድመ አያቶቹ እየተወራረሰ የመጣውን ደግ ደጉን ባህሉን እያስጠበቀ ለመሄድ በሚያደርገው ጥረት ዘመናዊው ዘመን ተግዳሮት እየሆነበት የተቸገረ ይመስለኛል፡፡ ደግነታችን፣ መተሳሰባችን፣ ከኔ ይልቅ አንተ መባባላችን፣ የሰውን ያለመፈለግ ቱባው የእምነትና የባህል ቅልቅሉ አስተሳሰባችን ወዘተ. ጠቃሚ ባህሎቻችንን ጠብቀን እራሳችንን ማዘመን የማይቻል ያህል ጥሩ ጥሩውን እያስወገድን ከሽቀጦች ጋር የሚመጡትንና ከማንነታችን ጋር የማይስማሙትን የወዲያኛዎቹን ባህልና አስተሳሰብ በእጃችንና በልባችንም ጭምር ማስገባት ከጀመርን ውለን አድረናል፡፡

አንድ ወቅት ላይ ለሥራ የሄድኩበት ገጠር ቀበሌ ያየሁት ነገር ሁሌም እራሴን ስለታማኝነቴ እንድጠይቅ ያደርገኛል፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው እኔና ለስራዬ በረዳትነት የተመደበልኝ የአካባቢው ሰው ቀጭኑን የገጠር ቀበሌ የእግር መንገድ ተከትለን ወደምንፈልገው ቦታ በመጓዝ ላይ ሳለን ከመንገዳችን ላይ ውስጡ በተለያዩ እቃዎች የታጨቀ ዘንቢል በላዩ ላይ ቁራጭ እንጨት እንደዋዛ ጣል ተደርጎበት ተመለከትን፡፡ ከኔ ፊት ላይ የመገረም ምልክት ሲታይ አብሮኝ ካለው ረዳቴ (መንገድ መሪዬ) ዘንድ ግን ምንም ዓይነት ስሜት ላነብ አልቻልኩም፡ ፡ መገረሜን ያስተዋለው ረዳቴ ግና ቀልጣፋ ኖሮ «ይህ የምታየው ዕቃ ከገበያ የመጡ ሰዎች ሸክም ሲከብድባቸው አስቀምጠውት የሄዱት ነው፡፡» አለኝ ለኔ ችግሬ መቀመጡ ሳይሆን የተቀመጠበት አካባቢ ምንም አይነት ሰው አለመኖሩና በማን ሊጠበቅ እንደሚችል ማወቅ ነው፡፡ አሁንም ግርታዬ የገባው ይሄው አጣማጄ «ስማማ እዚህ ከሰው በላይ ከላይ የሚያየውን ፈጣሪ የሚፈራ ህዝብ ስለሆነ ያለው ይሄን የምታየውን ዕቃ ባለቤቶቹ ቤታቸው ሲደርሱ ሰው ሰደው ያስወስዱታል እስከዚያው ግን ማንም አይነካውም ምክያቱም የሰው ነገር መዳፈር ባህላችንም አይደለም፡፡» ነበር ያለኝ፡፡

እስቲ ልብ በሉ አይደለም ከመንገድ ዳር የተቀመጠና ጠባቂ የሌለው ዕቃ ከአፍ ውስጥ ምራቅ የመስረቅ ያህል ፈጣን ነጣቂዎች ባሉበት ከከተሜዎች ዘንድ እየኖርኩ ይሄ የገጠመኝ የገጠሬዎቹ ኩናቴ እንዴት አይገርመኝ?፡፡ ዓለማችን የስግብግቦች መጠራቀሚያ የሆነች እስክትመስል ድረስ ኑሮዬ ይበቃኛልን ወደ ጎን ትቶ ከጥጋቡ በላይ ለመጥገብ በሰው ህልውና እጁን የሚሰደው አዳሜ በእውነት የያኔዎቹና የታማኞቹ አባቶቻችን የአብራክ ክፋይ ነው የሚል ጥያቄን ማስነሳቱ አይቀሬ ነው፡፡ ዛሬ የዘሩት ነገ መብቀሉ አይቀሬ መሆኑ የአደባባይ ሀቅ ነው፡፡ የተለያዩ ሀገራትን የስነ-ምግባር ጥሰቶች ስንመለከት ዓይነቱና መጠኑ እንደየሀገራቱ ይለያይ እንጂ ከስሩ ጉዳዩን ለመረመረና ነገሬ ብሎ ላጠና በነፃነት ስም የተተወ ትውልድ ውጤት መሆኑን ማወቁ አይቀርም፡፡ መብትና ግዴታን ሳይሆን መብቱን ብቻ እየነገርነው ያሳደግነው፣ ግለኝነትን እየተነፈስንበት ካንተ ወዲያ ላሳር ያልነው ወዘተ. የትናንት አበባ የዛሬ ፍሬ ውጤታችን ነው ይሄ ትውልድ፡፡

. . . ከአፍ ውስጥ ምራቅ

የመስረቅ ያህል

ፈጣን ነጣቂዎች ባሉበት . . .

ህዝብ አምኖና መርጧቸው ባስቀመጣቸው ወንበር ላይ ሆነው ከአስተሳሰባቸው ይልቅ እጃቸው ረዝሞ የሀገርን ጥሪት በስግብግብነት ሲዝቁ፣ በጉዳይ አስፈፃሚዎቻቸው በኩል ከባለጉዳዮች ኪስ ያለመራራት ገንዘብ ሲያወጡ፣ በስግብግብነት መንፈስ ከራሳቸው አልፈው በልጆቻቸውና በዘመድ አዝማዶቻቸው ስም በጥሬና በብስል ሀብት ሲያከማቹ ብቻ ምን አለፋችሁ ያልጠግብ ባይነት መንፈስ የተጠናወታቸው እነ ሆድ አምላኩን ስንመለከት የሀገራችን የወደፊት እጣ ፋንታ ሀሳብ ላይ ይጥለናል፡፡ ለዚህም ነው መንግስት እንዲህ አይነቶቹን ስግብግቦች በማደን ለፍትህ እያቀረበ ያለው፡፡

ከትንሽ እስከ ትልቁ አፉ ላይ ቀሎት የሚጠራውና ስያሜው በዝርዝር ሲታይ ሰፊ ትንታኔ የሚሰጠው ሌብነት አሊያም በዳቦ ስሙ ሙስና ተፈጥሮውን ስንቃኝ ለዘመናት የነበረ የማህበረሰብ ክስተት ነው፡፡ ሙስና እንደ አንድ በሽታ ሁሌም ከማህበረሰቡ ዘንድ ይነስም ይብዛ የሚኖር ሲሆን እንደ ተላላፊ በሽታዎች ሁሉ ልንከላከለውና ልንቆጣጠረው የማንችለው ጉዳይ አይደለም፡፡ የዚህ የሙስና መንስኤዎቹ ደግሞ ከስነ-ምግባርና የባህል መበላሸት ባሻገር መዋቅራዊ ችግሮችም ናቸው፡፡ ብልጥግናን መሻት የየትኛውም ጤናማና የሰብአዊ ሰው ተፈጥሮዋዊ ምኞት ሲሆን ሰዎች ግን ይህንን ጤናማ ምኞት ለማስፈፀም የሚጠቀሙት ኢፍትሀዊ መንገድ ሙስና/ሌብነት ቢባል የሚያስኬድ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር አላግባብ ከሚገኝ ብልጥግና ሌላ ስራን በአግባቡ አለመፈፀም፣ የህዝብና የመንግስትን አደራ መጣስና በተቀመጡበት የስልጣን ወንበር በአግባቡ ዜጋን አለመጥቀምን ወዘተ. ያጠቃልላል፡፡

አንድ ወቅት ላይ በኢቲቪ ያየሁት የስነ-ምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽን ያዘጋጀው ማስታወቂያ ልብን የሚነካና እኛ ትላልቆቹ ለትውልዱ ምን እያስተማርን እንደሆነ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ በመሆኑ ከልቤ ወድጄዋለሁ፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው አንዱ ህፃን ባለስልጣን ሌላው ደግሞ ባለጉዳይ ይሆኑና ባለ ጉዳዩ የእጅ መንሻ ለባለስልጣኑ ይዞ ሲመጣ የሚያሳይ ሲሆን እነዚህ ልጆች ይህንን ጨዋታ በህልማቸው ያዩት ሳይሆን በትክክል የአንደኛው ልጅ አባት ሲያደርገው የታየ ነበር፡፡ ታዲያ ሚዲያውን ካጨናነቁትና ፀረ ትውልድ ከሆኑ አንዳንድ ማስታወቂያዎቻችን ይልቅ እንዲህ ዓይነት ትውልድን ገንቢ ማስታወቂያዎችና ፕሮግራሞች እየተሰሩ ለታዳጊዎቻችን ቢቀርቡልን ትውልዱን የሙስና/የሌብነት ተጠቂ ከመሆን አዳነውም ማለት አይደል?፡፡

በዚህ ዙሪያ የስነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሲሠራ የነበረው ሥራ በርግጥም ትላልቆቹን ሙሰኞች አድኖ ለፍትህ ከማቅረብ ባሻገር ችግሩን ከምንጩ ለማድረቅ የነገ ሀገር ተረካቢዎች ላይም ያተኮረ ቢሆን ኖሮ በርቱ የሚያስብል ነበር፡፡ ምንም እንኳን ተቋሙ ብቻውን ይህን ሥራ የማይሰራና ትምህርት ሚኒስቴር ካሪኩለም ቀርፆ እንደ አንድ የትምህርት ዘርፍ ስነ-ዜጋ በሚል ተማሪዎች እንዲማሩ እያደረገ የሚገኝ ቢሆንም የስነ-ምግባና ፀረ-ሙስና ኮሚሽንም በበኩሉ በየ ትምህርት ቤቶች ክበባትን በማቋቋም ሙስናን የሚጠየፍ ዜጋ የማፍራትን ጉዳይ አጠናክሮ ሠርቶ ቢሆን ከፊት የሚመጣው ትውልድ መቶ ፐርሰንት ባይባልም በጥቂቱም ቢሆን ሌብነትን ወይም በዳቦ ስሙ ሙስናን መጠየፍና መዋጋት የሚችል ይሆንና ትንሽም ቢሆን እርፍ እንል ነበር፡፡

ዛሬ ከጎበዝ ተማሪ መኮረጅን እንደ ሀሪፍነት የተረዳ ተማሪ ነገ በሚሰጠው ቦታ ላይ ከባለ ጉዳዮች ላይ እጅ መንሻ ላለመቀበሉ ምን ማስተማመኛ ይኖረናል?፡ ፡ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ቤተሰቦቹ የኑሮ ከፍታ ላይ ለመውጣት ሌላውን ዜጋ መፈናጠጫ ሲያደርጉ የሚመለከት ህፃን የጊዜን እርካብ ተቆናጦ እሱም በተራው ሙሉ ሰው ወደ መሆን ሲደርስ ቤተሰቦቹ ገና በብላቴናነቱ በቀረፁበት የስህተት ጎዳና ላይ ቢሄድ ምን ሊገርመን፡፡

ማህበረሰባችን «ጫጩት ፊት ፈንግል አይወራም» የምትል አንድ ምርጥ አባባል አለችው በርግጥም ጫጩት ፊት ፈንግል ማውራት ለጫጩቶቹ አለማሰብ ነው፡፡ ታዲያ ለዶሮ ጫጩት አስቦ ከዘመናት በፊት ይህንን አባባል ያፀደቀው ወገኔ ለሙስና/ሌብነት ፊት ሰጥቶ በልጆቹ ፊት በእርጥብ አዕምሯቸው ላይ እየተረማመደ ስግብግብነትን ማስተማሩ ለምን ይሆን?፡፡ ኖር በሞቴ ብሎ ካለው ቁርሶ ከማካፈል በቀር የሰው ወርቅ አያደምቅ አባባሉን እያለ ያለችውን ጎርሶ ፈጣሪውን እያመሰገነና ሆድን የፈጠረ እራሱ ለነገ ያስባልን እየፀለየ የኖረውን ወገኔን ዛሬ ዛሬ ምን ክፉ ገብቶት አፍ ላይ የሚቀል ለህሊና የሚከብደውን ሙስናን/ሌብነትን ማስተናገድ ቻለ?፡፡

እንግዲህ እንደ ከተማችንም ሆነ እንደ ሀገር አቀፍ በሙስና ላይ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ይበል እሰየው ሊያሰኙ እና መጠናቸውን እያሰፉ ተደራሽነታቸውን ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊጨምሩ ይገባል፡፡ በተገኘው የህግ ድጋፍም ቀድሞ በመንግስት ተቋማት እና የልማት ድርጅቶች ላይ ብቻ ይሠራ የነበረውን ሥራ በግሉ ዘርፍ ወደ ሚገኙትም ህዝባዊ ድርጅቶች ለማስፋፋት አቅም አግኝቷል፡ ፡ ይህ በጥር/2007 ዓ/ም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመቅረብ የፀደቀው የማሻሻያ ህግ በዘርፉ ሙስና ሊፈፀም ሲልና ተፈፅሞ ሲገኝ ጥፋተኞችን በመመርመርና በመክሰስ ህግ ፊት ለማቅረብ፤ የሙሰኞችን ሀብትና ንብረት በፍርድ ቤት ትእዛዝ ለማሳገድ፤ በሙሰኞች የተመዘበረን ሀብትና ንብረት ተመጣጣኙን ለማስመለስ፤ በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ ተቋማትን የአሠራር ሥርዓት በማጥናት ክፍተቶችን በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ ለማቅረብ እንዲሁም ለጠቋሚዎችና ምስክሮች ከለላ ለመስጠት ያስችላል፡፡

ያ ቢሆንም ጉዳዩ «ሀምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ፤ ለሀምሳ ሰው ጌጡ» እንዲሉ ነውና የተጀመረውን መልካም ሩጫ በመከተል እኛም የሌብነት/የሙስና ገፈት ቀማሽ ዜጎች ከመንግስት ጎን በመቆም ልንተጋ ይገባል፡ ፡ እኮ በምን በምን ቢሉ በየትምህርት ቤቱ የነገ ሀገር ተረካቢ ህፃናትና ወጣቶችን ሊጋውን አዕምሮዋቸውን ጤናማና ስነ-ምግባር ተኮር የሆነ እውቀትን በመለገስ እንዲሁም መልካም እሴቶቻችንን እንዲያውቁ በማድረግ የድርሻችንን ልንወጣ ግድ ነው፡፡

ሙስና በባህሪው ተጋቦሽ በመሆኑና አንድ የሆነ ቦታ መገታት ካልቻለ እንደ ካንሰር እየተስፋፋ የሚሄድ በመሆኑ ልክ ኤች አይ ቪ ኤድስ ላይ እንደተደረገው ዘመቻ ሁሉ ትውልድ ይዳን በኛ ይብቃ ብሎ ተተኪው ትውልድ ላይ የሚሠራ ዜጋ አስፈላጊ ነው፡፡ መንግስት ከሰሞኑ በጉዳዩ ላይ እየወሰደ ያለው እርምጃ ይበል የሚያሰኝና በህብረተሰቡ መካከል የተሰገሰገውን የተንጠልጣይነት አስተሳሰብ ለማስወገድ ደግሞም ቆም ብለው ማሰብና ግራቀኙን ማየት የዕድሜ ጫፋቸው ገና የማይፈቅድላቸውን የነገ ሀገር ተረካቢ ዜጎች ትኩረት አድርጎ መስራትም ቢጀመር በርግጥም ነገሩን ሳይቃጠል በቅጠል እንድንል ያደርገናል፡፡

መንግስት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ቁልፍ ቁልፍ ቦታ ያሉና ምናልባትም አይነኬ መስለው የሚታዩ ትላልቅ ባለስለጣናትን ተጠያቂ በማድረግ ለህግ አቅርቦ አስፈላጊውን ቅጣት እንዲያገኙ የማድረግ ጅማሮውን ተያይዞታል፡፡ በርግጥ ጅማሮ እንደመሆኑ መጠን ገና ብዙ ይቀረዋል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን የብልሹ አሰራር፣ ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት አብይ ምክኒያት የስነ-ምግባር ጉድለት ስለሆነ ወጣቶችና ህፃናትን ገና ከለጋነታቸው በመልካም ስነ-ምግባር ማነፁን ስራዬ ብሎ መሥራት ጊዜ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ መሆን የለበትም፡፡

እነዚህን ህፃናትና ወጣቶች በመልካም ስነ-ምግባር ማነፅ ጠቀሜታው በሀገራችን ህፃናትና ወጣቶች አብዛኛውን የህብረተሰብ ክፍል የሚሸፍኑ በመሆኑ ለነገዋ ኢትዮጲያ ባህላዊ ኢኮኖሚያዊና ዲሞክራያዊ ግንባታ ሰፊ ድርሻ ስላላቸውና ስለሚኖራቸው የተሰጣቸውን ኃላፊነት በመልካም ስነ-ምግባር እንዲወጡ፤ ለተለያዩ ማህበራዊ ባህላዊና የቴክኖሎጂ ለውጦች በቀላሉ የሚጋለጡ በመሆናቸው ስነ-ምግባራቸውን ሊያበላሹ ከሚችሉና ለሌብነት/ለሙስና ሊያጋልጧቸው ከሚችሉ አጋጣሚዎች መቆጠብ እንዲችሉ፤ በሁሉም ማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ (በተማሪነት አሊያም በአንድ ተቋም አገልግሎት ፈላጊ በመሆን ወይም ሰራተኛ በመሆን) የሚገኙ በመሆኑ፤ እንቅስቃሴያቸው በመልካም ስነ-ምግባር የተገነባ እንዲሆን፣ በእያንዳንዷ እንቅስቃሴ ውስጥ በሚወስኑት ውሳኔ ራሳቸውን ፣ወገናቸውንና ሀገራቸውን የሚጠቅም ምክኒያታዊና ሚዛናዊ ውሳኔ መስጠት እንዲችሉ፤ በአቋራጭ ሳይሆን ሠርቶ ማደግና መለወጥ እንደሚቻል እንዲገነዘቡ፤ ትልቁን ዳቦ ለኔ የሚል እሳቤን ይዘው እንዳያድጉ ወዘተ. . . መንግስት፣ የሃይማኖት ተቋማትና ህብረተሰቡ በባለ ዳቦ ስሙ ሌብነት/ሙስና ዙሪያ ፅዩፍነቱን በሚገባ በመተንተንና በማውገዝ ትምህርት ሊሰጡ ይገባል፡፡

በርግጥም ሁላችንም ከላይ በተጠቀሰው መሰረት የሀገር ነቀርሳ በሆነው በሌብነት/ሙስና ላይ በዘመቻ ጦርነት ብንከፍት፤ ነገርን ከስሩ ውሀን ከጥሩ እንዲል የሀገሬ ሰው ገና ከጠዋታቸው ሀይ ቢሏቸው ሊሰሙ የሚችሉ አበባዎቻችን ላይ ትኩረት በማድረግ በቤታችን፣ በትምህርት ቤቶች፣ በአገልግሎት መስጫ ተቋማቶቻችን ወዘተ. ከአያገባኝም መንፈስ ተላቀን በታዳጊዎች ላይ ልንሰራ እንደሚገባን ብናምን ታዳጊዎቻችንንም ገና ከጠዋታቸው «ትልቁን ዳቦ ለኔ» የሚል ስግብግብ አስተሳሰብንና ለሀገርም ሆነ ለራሳቸው ጠንቅ የሆነ ሌብነትን እንደ ብልጠት አሊያም በኛ አባባል እንደ ሀሪፍነት ተቀብለውት በውስጠ ልቦናቸው አፅድቀውት እንዳያድጉ ሚናው ከፍተኛ ነው፡፡ እኔ የኔን በዚህ ላብቃ ከሌብነት ወይም በዳቦ ስሙ ከሙስና ጋር የተጀመረው ግብግብ ግን ይቀጥላል፡፡

ውድ አንባቢዎቼ በቀጣይ ሳምንት ስለሙስና የሚተነትነውን የዚህኑ ፅሁፍ ሁለተኛ ክፍል ይዤ እመለሳለሁ፡፡ ታዲያ ልብ በሉ ቀጠሯችን ከነብሳችን ጋር አይደለም ምክያቱም ነብሳችን በእጃችን ያለች ሃብታችን ስላልሆነች ለማለት ያክል ነው፡፡ ዕድሜ ከተቀጠለልን ሳምንት በቸር ያገናኘን፡፡ ሰላም ለሀገራችን!!

## የአለም . . .

ከገጽ 1 የዞረ

በመድረኩ የሃይማኖት አባቶች ከሀይማኖቱ ጋር በማያያዝ ለመድረኩ ተሳታፊዎች ትምህርት በመስጠት በፀሎት የውይይት መድረኩን ከፍተዋል።

በፓናል ውይይቱ መልዕክት ያስተላለፉት የድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዩሱፍ ሰኢድ እንደተናገሩት በሀገር አቀፍ ደረጃ ካለው የኤች አይ ቪ ኤድስ ስርጭት ድሬዳዋ በ3 ኛነት ደረጃ በመገኘቷ የጤናና ማህበራዊ ቀውስ እጅግ ከፍተኛ ነው ብለዋል።

ምክትል ቢሮ ኃላፊው ከዚህም ጋር በማያያዝ ማህበረሰቡ ተመርምሮ እራሱን በማወቅ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ከተገኘ የህክምናና ሌሎች ተያያዥ ክትትሎችን በሚገባና ሳያቋርጡ ማድረግ እንዲቻል፤ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ ግብረሰናይ ድርጅቶች፣ ማህበራትና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በስፋት እና በመናበብ በመሥራት ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከል የሚሠራውን ሥራ በኃላፊነትና በየኔነት መንፈስ ሊያግዙ እንደሚገባም አሳስበዋል።

በድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ጀማል አህመድ በበኩላቸው የዘንድሮው የዓለም ኤድስ ቀን “በላቀ የማህበረሰብ ተሳትፎ ኤች አይ ቪን እንግታ” በሚል መሪ ቃል ስናከብር ማህበረሰቡ ኤች.አይ.ቪን በመከላከል እና በመቆጣጠር ረገድ በአግባቡ ኃላፊነቱን እንዲወጣ እና ኤድስን በ2030 የማይተላለፍበት ደረጃ ለማድረስ ለተያዘው ግብ ማህበረሰቡ የመሪነት ሚናውን እንዲወጣ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ቃል የምንገባበት ቀን ነው ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ጀማል ገለፃም ላለፉት ዓመታት ኤች.አይ.ቪን በመከላከል እና በመቆጣጠር ረገድ የተሻለ ውጤቶች መመዝገቡን እና ለአብነትም አዲስ በኤች.አይ.ቪ የሚያዙ ሰዎች በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ መቻሉን እንዲሁም በኤድስ ምክንያት የሚከሰትን የሞት መጠን በ2010 ከነበረበት በ2022 በ52 በመቶ ዝቅ ማድረግ መቻሉን ገልፀዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኤች አይ ቪ ኤድስ ከእናት ወደ ልጅ የመተላለፍ መጠኑን እ.አ.አ 2010 ከነበረበት 46% እ.አ.አ 2022 ወደ 12% እንዲቀንስ ተደርጓል ብለዋል። የገጠሙ ተግዳሮቶችን ለመሻገርና ኤች.አይ.ቪን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በሚደረገው ጥረት ማህበረሰቡ የማይተካ ሚና ያለው በመሆኑ ለኤች.አይ.ቪ መከላከል ፕሮግራሞች አተገባበር የበኩላቸውን ሚና እንዲያበረክቱም አቶ ጀማል ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

የኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ እያስከተለ ያለውን ማህበራዊ የጤና ችግሮች እና በኢኮኖሚው ዙሪያ እያስከተለ ያለው ጫና እንደ ሀገር ያለውን ነባራዊ ሁኔታ የዳሰሰ የመወያያ ሰነድም ቀርቦ ሰፊ ውይይት ተደርጎበታል።

# ገብረ ክርስቶስ ገጣሚው


በትዕግሥት ወልዴ

ገብረ ክርስቶስ ደስታ ጥር 5 ቀን 1924 ዓ.ም በሀረር ከተማ ተወለደ ፡፡ አባቱ አለቃ ደስታ በስተርጅና የወለዱት የቤተሰቡ የመጨረሻ ልጅ ነው ፡፡ የገብረ ክርስቶስ የህጻንነት እድሜ እንደ ሌሎች ህጻናት በጨዋታ የተሞላ አልነበረም፡፡ በተወለደ በመንፈቁ እናቱ ወይዘሮ ዐፀደማርያም በሞት ተለዩ ፡፡ ወይዘሮ አበበች ወልደሃና የተባሉ ሞግዚትም ተቀጠሩለት እና እንደ እናት እየተንከባከቡ አሳደጉት ፡፡ ፋሽስት ጣሊያን በወልወል ግጭት ሰበብ ሃረርን በመውረሩ ምክኒያት ከሃረር አዲስ አበባ በ 3 አመቱ ተሰደደ ። ገብረ ክርስቶስ ደስታ በልጅነት ከገጠሙት መራር ሃዘኖች መሃከል ከቤተሰቡ መለየቱ እና አባቱ በጣሊያን መወሰዳቸው ነው ። ከዚያም ታላቅ እኅቱ አየለች ደስታ ዘንድ አዲስ አበባ መጣ ፡፡ ፡ ይሁን እና በድጋሚ ከአዲስ አበባ ሃረር በመመለስ የቀለም ትምህርቱን በራስ መኮንን ትምህርት ቤት መከታተል ጀመረ ። ምንም እንኳን ቤተሰቡ ገበሬ እንዲሆን ቢመኙም ገብረ ክርስቶስ ግን የነብስ ጥሪውን ለማሳካት በ 6 አመቱ ስዕልን በሚያገኘው እርሳስና ወረቀት መሣሣል ጀመረ ፡፡ ገብረክርስቶስን በልጅነቱ በቅርብ የሚያውቀው ሰይፉ መታፈሪያ እንደተናገረው ገብረ ክርስቶስን የማውቀው ከትምህርት ቤቱ ጀምሬ ነው ። እዚያ ባዶ እግራችንን፣ በቴኒስ ኳስ ኳስ ተጫውተናል።

...ከእለታት ባንዱ ቀን ግን፣ ዕረፍት ወጥተን ፣ ግማሹ በሚሯሯጥበት፣ ግማሹም ኳስ በሚጫወትበት ሽብር ኹኔታ ውስጥ፣ ገብረክርስቶስ ጥግ ተቀምጦ፣ ቁምጣ ሱሪውን አጋልጦ ባዶ ጭኑ ላይ ሥዕል ሲሠራ እንዳየሁት አስታውሳለሁ። እና አሁን መለስ ብዬ ሳስብ ሥዕል ምንኛ ከልጅነቱ ከጭንቅላቱ ገብቶ ኖሯል እላለሁ። ለዚህም የአባቱ የአለቃ ደስታ ነገዎ የድጉሥ፣ የቁም ጽሕፈትና የብራና መጻሕፍት ላይ ሥዕል ምን ያኽል ተፅዕኖ አድርጎበት ነበር ይሆን? በምንስ መንገድ? እላለሁ።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ በ1943 ዓ.ም አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ኮሌጅ ፣ ሳይንስ ፋኩልቲ፣ ባዮሎጂ ዲፓርትመንት ገባ፡፡ በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ መራራ ግጭት ገጠመው፡፡ በነፍሱ ሜዳ ላይ ሥነ-ጥበብና ሥነ-ሳይንስ ተፋለሙ ፡፡ በመጨረሻ ሥነ-ጥበብ አሸነፈች የኮሌጅ ትምህርቱን አቋርጦ ለመውጣት ተገደደ ለአራት ዓመታት ያህል የተለያዩ ስራዎችን ሲሰራ ቆየ ፡፡ በአውራ ጎዳና ባለሥልጣን፣ በሲንክላር የነዳጅ ድርጅት፣ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና በስብስቴ ነጋሢ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በተለያየ ጊዜ ተቀጥሮ ሠራ፡፡ በመጨረሻ ሥራ የሚባል ነገር እርግፍ አድርጎ በመተው በሥዕል ሥራው ብቻ ተጠመደ ፡፡

በ1946 ዓ.ም ዘመናዊ የአሣሣል ዘዴ የያዙ ሥዕሎችን ይዞ ብቅ አለ ፡፡ በ1949 ዓ.ም ኒውደልሂ ላይ በተደረገው ዓለም አቀፍ የሥዕል ትርኢት ላይ ለመሳተፍ ወደ ህንድ አቀና ፡፡ ከህንድ እንደተመለሰ በጠና ታምሞ ነበር ከህመሙ አገግሞ ሲነሳም ሕይወቱን ሙሉ ያልተለየው የለምጥ ምልክት ወጣበት፡፡ በዚህ ወቅት የሃያ አራት



ዓመት ወጣት ነበር - ሠዓሊና ገጣሚ ገብረክርስቶስ ደስታ !

በ1950 ዓ.ም ምዕራብ ጀርመን የሚገኝ አንድ የጥበብ አካዳሚ ነጻ የትምህርት ዕድል ስለሰጠው ምዕራብ ጀርመን ገባ፡፡ በዛም እያለ ህመሙ አገረሸበት ገጽታው ላይ የነበረው ለምጥ በጉልህ ሰውነቱ ላይ ወጣ ፡፡ የጀርመን ሐኪሞች ሊፈውሱት ጣሩ አልቻሉም ፡፡ ከሦስት ዓመታት በኋላ የጥበብ ትምህርቱን አጠናቅቆ ተመረቀ ፡፡ በ1953 ዓ.ም በጀርመን የሥነ-ጥበብ አፍቃሪያን ዘንድ ዝና ያተረፈለትን የሥዕል ኤግዚቢሽን አሳየ - በታሪካዊው ቬትሆቨን አዳራሽ አያሌ ኤግዚቢሽኖች ተከተሉ ፥ በጀርመን የሥነ-ጥበብ ማማ ላይ የወጣ የመጀመሪያው አፍሪቃዊ ሆነ ፡፡ በባዕድ ሀገር ትዝታና ናፍቆት አሰቃዩት ፡፡ ወደ ሀገሩ ተመለሰ፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰ በኃላ በሥነ-ጥበብ አስተማሪነት ተቀጥሮ እየሰራ ሳለም ለሥዕል ኤግዚቢሽን ለማሳየት አሜሪካ ተገኘ ፡፡ መጋቢት 21 ቀን 1973 ዓ.ም በተወለደ በ49 ዓመቱ ፣ አሜሪካ፣ አክላሆማ ግዛት አረፈ፡፡

“ለምለም ነው አገሬ፣

ውበት ነው አገሬ፣

ብሞት እሄዳለሁ ከመሬት ብገባ

እዚያው ነው ዐፈሩ፣ የማማ ያባባ፡፡”

ብሎ በቃላት ግጥም የሣለው ሠዓሊ ገብረ ክርስቶስ፣ ከሀገሩ መሬት ሳይገባ፣ ግብዐተ-መሬቱ እዛው አሜሪካ ተፈጸመ፡፡

ገብረ ክርስቶስ ደስታ “ሁለት-ዓይን” ሠዓሊ ነው፡ ፡ በቀለም ሥዕል ይሥላል፣ በቃላት ግጥም ይሥላል፡ ፡ ሥዕልና ግጥም ሠዓሊ ገብረ ክርስቶስ ደስታ የገብረክርስቶስ ግጥሞች ምዑዝ የቀለም ሽታ አላቸው ፡፡ የገብረ ክርስቶስ ግጥሞች – በመሠረቱ – ወል ስልታቸውን ቤት የሚመቱ ናቸው ፤ አልፈው አልፈው ግን ቤት ሳይመቱም ይገኛሉ ።

የገብረ ክርስቶስ ቤት መምቺያ ፊደሎች፣ ገና ሰፊ የጥናት ሥራ የሚጠይቁ ቢሆኑም የ ለ፣ ሰ፣ ረ፣ ተ፣ ነ ቤቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው ማለት ይቻላል።

ገብረ ክርስቶስ የተምሳሌት ባለጸጋ ነው።

እንደ ጽጌ-ረዳ

እንደ አደይ አበባ

እንደ ሎሚ ሽታ፡፡

እንደ ዕጣን ጢስ እንጨት፣ እንደ ከርቤ ብርጉድ

እኔ እወድሻለሁ

አበባ እንዳየ ንብ፡፡

እንደ ቢራቢሮ ጫካ እንደሚያስሰው

ፍቅርሽ በፍቅሬ በፍቅርሽ ልቅመሰው፡፡

የገብሬ ግጥሞች በወረቀት ሸራ ላይ በቃላት የተሣሉ፣ ገጽታቸው እንደ መፀው ጀምበር ፍንትው ብሎ የሚታይ ሥዕሎች ናቸው፡፡

የሚሽቀዳደሙት የባሕር ቅርድዶች ወደ አሸዋው ወጡ

የፀሐዩን ጮራ ይዘው እየሮጡ፡፡

ይርመሰመሳሉ፤ ይረባረባሉ

ያብረቀርቃሉ፡፡

ምንድን ነው ጉዳዩ

ነፍስ አስቆጥቶ የሚያሯሩጣቸው?

ተልከው ይሆናል አንድ ነገር ይዘው።

ከባሕሩ መሀል ዓሣው ሲነጋገር

ወይም ከሩቅ ጠረፍ መርከብ ሲሽከረከር

ወይም ከጀልባው ሥር፡፡

ማዶ ከሚታየው ከትንሹ ደሴት

ከተንዘራፈጠው ከጋራው አቀበት፡፡

ይዘዋል በመላ፡፡

ማን ያውቃል ምን ይሆን?

ትርጉሙ ረቂቅ ነው የቋንቋቸው መጠን

እነሱም አያውቁት /ይቻላል ለማለት/

ምን እንዳስነሳቸው አጥመልምሎ ድንገት፡፡

ምን እንደሚሠሩ የት እንደሚሄዱ

የፀሐዩን ጮራ ሲያመጡ ሲወስዱ፡፡

አሸዋ ሲገፉ

ዓሣን ሲሸከሙ ሲጥሩ ሲለፉ፡፡

ዛጎል አንከባለው ወደ ዳር ሲያወጡ

ሲጋጩ ሲሮጡ ።

ገብረ ክርስቶስ፣ እንደ ገጣሚ፣ የሐሳብ እምብርቱ ሰው ነው፤ ያገርና የወገን ፍቅር ነው፣ ሙዚቃ ነው፣ ዳንስ ነው፣ ተፈጥሮ ነው፣ ሮማንስ ነው፣ የባህል ፍቅር እና ወዘተ ነው። ዝርዝሩ ይሄ ሆኖ ሳለ ወሳኝ ሐሳቦችን የያዙት ግጥሞች የሚከተሉትን ጭብጦች ያካተቱ ስንኞችን ያቁለጨልጫሉ – እናንብባቸው፡-

የልጅነት ጊዜ ትምጣ ትዝታዬ

ድሮ የሠራችኝ አሁን መኖሪያዬ።

ዕንቆቅልሽ ነፍሴ ንገሪኝ በርጋታ

ጨንቆኛል ጠቦኛል ያለሽበት ቦታ።

(“ምንድነሽ”፣ ገጽ 61)

“አንድ ነገር ሲሆን ግዴታ መነሻው

መኖር ይገባዋል የሚቀሰቅሰው

ሰውንም ያስገኘ

መኖር ግድ አለበት ዓለምን የናኘ”

በማለት ብዙዎሽ ሲያቀርቡ ክርክር

እስማማለው በዚህ ያለመጠራጠር።

(“ደብዳቤ”፣ ገጽ 126-7)

.

ሞትን ያሸንፋል

ሁሉን ሲቆጣጠር እግዚአብሔር ይኾናል

ወዴት አለ እንቅፋት

የት አለና ዳገት

ለዚህ ትንሽ ተባይ

ገና ይራመዳል።

(“ይራመዳል”፣ ገጽ 132)

ከምብርቷ ዘላቂ

ምጥቃለምን

አይለቅ መንገዱን።

(“የጠፈር ባይተዋር” ገጽ 114)

## በሴቶች . . .

ከገጽ 1 የዞረ

የነጭ ሪቫን ዓላማውም በሴቶች ላይ የሚፈጸም የኃይል ጥቃት የወንጀል ድርጊት መሆኑን ማስገንዘብ፣ ወንዶችም የበኩላቸውን በጎ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ጥሪ ማስተላለፍ እና ሴቶችም የሚፈጸሙባቸውን የኃይል ጥቃቶችን በዝምታ እንዳያልፉ በማድረግ ዝምታውን መስበር ነው ብለዋል።

በየዓመቱም ይህ የነጭ ሪቫን ቀን አዋቂና ታዳጊ ወንዶች ይህንን የሰላም ተምሳሌት የሆነውን ነጭ ሪቫን እንዲያደርጉና በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ የኃይል ጥቃቶችን አስመልክቶ “በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት በዝምታ ላላልፍ ቃል እገባለሁ” በማለት ቃል እንዲገቡ የሚደረግበት የንቅናቄ ሳምንት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በሴቶችና ታዳጊ ሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች የተለያየ መልክ ቢኖራቸውም መገለጫቸው በዋነኛነት አካላዊ፣ ወሲባዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ አኮኖሚያዊ ጥቃት ናቸው። በተጨማሪም የስርዓተ-ጾታ እኩልነት አለመከበር፣ አድሎዓዊ እና የተዛቡ አመለካከቶች፣ ልማዶች እና ባህሎች መሆናቸውንም ተናግረዋል።

የፆታ ጥቃትን ለመከላከል ሊወሰድ የሚገባው የመፍትሄ እርምጃዎች ውስጥም፤ በቤተሰብ መካካል ያለው ግንኙነት በልጆቻቸው አመለካከት ላይ የሚያሳድረውን በጎም ሆነ መጥፎ ተጽእኖ በመረዳት የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ይኖርባቸዋል ብለዋል። እንዲሁም የሲቪክ ማህበራት በሥርዓተ ፆታ፣ በስነተዋልዶ፣ በሰብዓዊ መብቶችና በሴቶች መብቶች ዙሪያ ህብረተሰቡን በማስተማርና የአድቮኬሲ ሥራዎችን በመስራት ለችግሩ ህብረተሰቡን ያሳተፈ ዘላቂ መፍትሄ ለመሻት ሃላፊነት እንዳለባቸውም አሳስበዋል።

በተጨማሪም የሃይል ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች የህግ ጥበቃና አፋጣኝ ፍትህ እንዲያገኙ፣ ተጠቂዎችም የሚካሱበትን ሥርዓት መዘርጋትና ጠንካራ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር ለማድረግ እንዲሁም የሃይል ጥቃትን በመከላከል ላይ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ማበረታታትና በትብብር ለመስራት ቢሮው በትኩረት የሚሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

በመጨረሻም በድሬዳዋ አስተዳደር ያለዕድሜ ጋብቻን፣ የሴት ልጅ ግርዛትንና ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን እንዲሁም በሴቶችና ህጻናት ላይ የሚፈጸሙ የሃይል ጥቃት ወንጀሎችን አስመልክተው ማንኛውም የአስተዳደሩ ነዋሪ ሃሳቡን በነጻነት መግለጽ የሚቻልበት 8955 ነጻ የስልክ መስመር ላይ በመደወልና ጥቆማ በመስጠት ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ወ/ሮ ሁክሚያ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

ዘገባው የድሬዳዋ አስተዳደር ሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ህዝብ ግንኙነት ክፍል ነው፡፡

## ማስታወቂያ

በአመልካች ሁርጃ ሙሳ አህመድ እና በተጠሪ አቶ ሙሳ ኡመር ኡስማን መካከል ስላለው የባልና ሚስት ክስ ጉዳይ በተመለከተ ተጠሪ መከሰሱን አውቀው ቀርበው መከላከል እንዲችሉ ለታህሳስ 2 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡30 ለሆነው ቀነ ቀጠሮ እንዲቀርቡ የድ/ዳ የፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት 2ኛ ቤተሰብ ችሎት አዟል፡፡

**የድ/ዳ የፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት**

## ማስታወቂያ

**ለአቶ አብዲ ሠኢድ**

**ባሉበት**

አመልካች ወ/ሮ ደህቦ ጀማል በዚህ ፍ/ቤት ቀርበው በእርሶ ላይ እርሶ የሉም በማለት የፍቺ ክስ የተመሰረተቦት ስለሆነ እርሶ አልያም ይህን የፍቺ ክስ አቤቱታ ተቃዋሚ ካለ ለ01/04/2016 ዓ/ም ለሆነ ቀጠሮ እንዲቀርቡ ፤ባይቀርቡ ግን በሌሉበት ፍ/ቤቱ የፍቺ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ያሳውቃል፡፡

**የፌ/መ/ደ/ሸ/ፍ/ቤት**

# ዛሬም እንደ ትላንቱ ትኩረታችንን የሚሻው የጋራ ጉዳያችን !

በሔኖክ ይልማ

በመላው ዓለም የበርካቶችን ሕይወት ሲቀጥፍ 40 ዓመታት ተቆጥረዋል። ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ የብዙዎች ትኩረት የኮሮና ቫይረስ ላይ ቢሆንም ዛሬም የብዙዎች ስጋት ነው ኤች አይ ቪ ኤድስ። በተለይ አፍሪቃ ውስጥ ከ25 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ የዚህ በሽታ ተጠቂ ነው።

በዓለም ደረጃ የኤች አይ ቪ ቫይረስ ስርጭትን ለመግታት በተጀመረው ጥረት ብዙ ስኬቶች ቢገኙም አሁንም ሙሉ ለሙሉ ለማሳካት የሚቀሩ ነገሮች መኖራቸውን የዓለም የጤና ድርጅት አመልክቷል።

በጎሮጎሳውያን የጊዜ ቀመር 1981 ዓ,ም ነበር አሜሪካውያን ዶክተሮች ምንነቱ ያልታወቀ ህመም በተወሰኑ ወጣት ወንዶች ላይ አገኙ። በሽታው ምንነቱ ሳይታወቅ በፊት ለየት ያለ የሳንባ መቆጣት ተደርጎ ነበር የተወሰደው። ስሙ ባልታወቀው በሽታ የሚያዙ ታማሚዎች ትኩሳት የሚያጠቃቸው ሲሆን የዕጢዎች መቆጣትም እንደሚታይባቸው ቆየት ያሉ ጥናቶች ያሳያሉ። በበሽታው ብዙ ወንዶች እና ሴቶች ከሞቱ በኋላ በዓመቱ አኳየርድ ኢሚዩን ዲፊሸንሲ ሲንድሮም በምህጻሩ ኤድስ የሚል ስያሜ አገኙ። የሰውን በሽታ የመቋቋም አቅም የሚያጠቃው HIV ተሐዋሲ ተገቢውን የህክምና ክትትል ካላገኘ ወደ ኤድስ እንደሚሸጋገር የዘርፉ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ።

የዓለም የኤድስ ቀንን በጎሮጎሳውያን ጊዜ ቀመር 1988 ዓ,ም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲታሰብ ሲያደርግ ተሐዋሲው በዚህ ጊዜ ከ100 በሚበልጡ ሃገራት ተዳርሶ ነበር። ከዚህ ጊዜ አንስቶም በየዓመቱ ኅዳር 22 ቀን ዕለቱ ይዘከር ጀመር። የዘንድሮው መሪ ቃል "የማህበረሰብ መሪነት ለላቀ ኤች አይ ቪ መከላከል" የሚል ነው። ማህበረሰቡ ኤች.አይ.ቪን በመከላከል ረገድ የሚጫወተው የማይተካ ሚና በአገር አቀፍ ደረጃና እስከታች ባለው የመንግስት መዋቅርና በማህበረሰብ አደረጃጀት ዕውቅና የሚሰጥበት ብቻ ሳይሆን በቀጣይ ማህበረሰቡን በማብቃት ወደ መሪነት ደረጃ ለማምጣት እንዲሁም የመሪነት ሚናውን እንዲወጣ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ቃል የሚገባበት ቀን ነው፡፡

መላውን ዓለም ያዳረሰው ኤች አይ ቪ በተለይ አፍሪቃን ክፉኛ መጉዳቱ የተመዘገበ ዕውነታ ነው። ከ25,5 ሚሊየን ሕዝብ በላይ በቫይረሱ መያዛቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ። ተሐዋሲው በተስፋፋባቸው ከሰሃራ በስተደቡብ በሚገኙ ሃገራት በተለይ ደቡብ አፍሪቃ፣ ስዋዚላንድ፣ ቦትስዋና፣ ሌሴቶ፤ ማላዊ፣ ናሚቢያ፣ ናይጀሪያ፣ ኬንያ እና ዚምባቡዌ ክፉኛ ተጎድተዋል።

ማህበረሰቡ በኤች.አይ.ቪ መከላከልና መቆጣጠር ፕሮግራም ዕቅድ ዝግጅት፣ትግበራ፣ ክትትል እና ግምገማ እንዲሁም ሃብት ማሰባሰብና አስተዳደር ላይ የመሪነት ሚናውን እንዲወጣ የማስቻል ሚና አለው፡፡ በቂ እና ቀጣይነት ያለው የህብት ድጋፍ በማድረግ ማህበረሰቡ በኤች አይ ቪ መከላከልና መቆጣጠር ፕሮግራም ላይ ያለው የመሪነት ሚና እንዲወጣ ማስቻል፣ማህበረሰቡ በኤች አይ ቪ መከላከልና መቆጣጠር ፕሮግራም የመሪነት ሚናውን እንዳይወጣ የሚያደርጉ መሰናክሎችን በማስወገድ አስቻይ ሁኔታዎችን መፍጠር፣ ኤች.አይ.ቪ በደማቸዉ ያለባቸዉ ሰዎች ላይ በስራ ቦታ እና በማህበራዊ ህይወት የሚደርሰዉን የአድሎና መገለልን ማስቀረትም ኤድስን ለመግታት የማህበረሰቡ ሚናዎች ናቸው፡፡

በሃገር አቀፍ ደረጃ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭት 0.9% ቢሆንም፤ የቫይረሱ ስርጭት ከቦታ ቦታ እንዲሁም ከማህበረሰብ ማህበረሰብ ከፍተኛ ልዩነት ያሳያል፡፡ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በጾታ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ልዩነትና በተሰማሩበት የሥራ ባህሪያቸው ምክንያት የኤች.አይ.ቪ ተጋላጭነታቸው ይለያያል፡፡ የስርጭቱ ሁኔታ በጾታ ሲታይ 60 % የኤች. አይ.ቪ ስርጭት በሴቶች ላይ ይታያል፡፡ በከተማ ያለዉ የኤች.አይ.ቪ ስርጭት ከገጠር አንፃር ሲታይ በከተማ ያለዉ የኤች.አይ.ቪ ስርጭት በሰባት እጥፍ ከፍ ያለ ነዉ፡፡

ኤች አይ ቪ በደማቸው ይገኛል ተብሎ ከሚገመቱ ወገኖች መካከል 84 በመቶ የሚሆኑት ተመርምረው ራሳቸውን እንዲያውቁና ከእነዚህ መካከል 98 በመቶ ያህሉን ደግሞ የፀረ-ኤችአይቪ መድሀኒት እንዲጠቀሙና መድኃኒት ከሚወስዱት ውስጥ 96.3 በመቶ ያህሉን የቫይረስ ልኬት መጠን በሚፈለገው መጠን እንዲወርድ ማድረግ ተችሏል (2022 HIV spectrium) ፣በዓመት ውስጥ የሚኖረውን በኤድስ ምክንያት የሚከሰትን ሞት መጠን በ2010 ከነበረበት 125/100,000 በ2022 ወደ 11/100,000 በማውረድ ከ52 ከመቶ በላይ መቀነስ ተችሏል (2022 HIV spectrium) ፣ኤችአይቪ ከእናት ወደ ልጅ የመተላለፍ ምጣኔ እ.ኤ.አ በ2010 ከነበረበት 46%እ.ኤ.አ በ2022 ወደ 12% በመቶ እንዲቀንስ ተደርጓል (2022 HIV spectrium)፡ ፡ ኤችአይቪ በደማቸው የሚገኝ ወገኖች ጥምረት ማህበራት በኤችአይቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ፕሮግራሞች ዕቅድ፣ ትግበራ፣ክትትልና ግምገማ ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ እንዲያረጉና የበኩላቸውን አስተዋፆ እንዲያበረክቱ መደረጉ፣ ኤችአይቪ በደማቸው ከሚገኝ እናቶች የሚወለዱ ህፃናት በወቅቱ የምርመራና ህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ የማፋጠኛ ዕቅድ በማዘጋጀት የተሰሩ ሥራዎች አበረታች መሆናቸው በሀገራችን የኤች.አይቪ.ኤድስ መከላከል እና መቆጣጠር ስራዎች የተመዘገቡ ውጤቶች ናቸው፡፡

ከዚህ ቀደም በየደረጃዉ የነበረው የአመራሩ ቁርጠኝነት ዛሬ ላይ መታየት አለመቻል (ለምሳሌ ፡ -ተቋማት የኤችአይቪ/ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ ፕሮግራሞችን በባለቤትነት አለመተግበር)፣ በኤችአይቪ መከላከል በጥልቅ የባህሪ ለውጥ ተግባቦት ስራዎች የተደረሱ በተለይም ለኤችአይቪ ተጋላጭ በሆኑ ቦታዎች የሚሰሩ ሰራተኞች እና ለኤችአይቪ ተጋላጭ የሆኑ አፍላ እና ወጣት ሴቶች የኤችአይቪ ምርመራ አገልግሎት ተጠቃሚ ከማድረግ አንፃር የጎላ ክፍተት መኖሩ፣የኤችአይቪ ምርመራ አገልግሎት በመንግስትና እና የግል የጤና ተቋማት እንዲሁም ማህበረሰቡ ድረስ በመዝለቅ የተለያዩ የምርመራ ስልቶችን በመተግበር እየተሰጠ የሚገኝ ቢሆንም ቫይረሱ በደማቸው ያለ ሰዎችን ከማግኘት አንፃር የሚጠበቀውን ያህል ውጤታማ መሆን አለመቻሉ፤ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ከሚገኝ እናቶች የተወለዱ ህፃናትን በጊዜው የኤችአይቪ ምርመራ እንዲያገኙ በማድረግ በኩል ክፍተት መኖሩ፤ኤችአይቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ለማድረግ የተያዘውን ግብ ለማሳካት በሁሉም ባለድርሻ አካላት ተከታታይነት ያላቸዉ ፕሮግራሞች ቢተገበሩም ለኤችአይቪ ተጋላጭ የሆኑ ህጻናት የኤችአይቪ መከላከያ መድሃኒት ያገኙ ዝቅተኛ አፈፃፀም መሆኑ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

ለኤች.አይ.ቪ በይበልጥ ተጋላጭ ሆኖ የሚታዩት የህብረተሰብ ክፍሎች

የሴተኛ አዳሪዎች (23 %)፣አደንዛዥ እፅ በመርፌ የሚወስዱ ሰዎች (14 %)፣የህግ ታራሚዎች (4.2 %)፣ የትዳር አጋራቸዉ የሞተባቸዉ (11.5 %)፣ከትዳር አጋራቸዉ ጋር የተለያዩ/የተፋቱ (2.9 %)፣የረጅም ርቀት መኪና አሽከርካሪዎች (4.9 %)፣ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ የሚሰሩ ሰራተኞች፣ የአፍላ ወጣቶች ሴቶች እና ወጣቶች ሴቶች (እድሜያቸዉ ከ15-24)፣ መለዮ ለባሾች (1.2 %)፣ኤች.አይ.ቪ በደማቸዉ ያለባቸዉ ሰዎች የትዳር አጋር ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡

- ሁሉን አቀፍ የኤች.አይ.ቪ መከላከል አገልግሎቶችን በሶስት ዋና ዋና ዘርፎች ይጠቃለላሉ፡፡

I. የኤች.አይ.ቪ መከላከል (HIV Prevention Programs)

- ትምህርታዊ ፕሮግራሞች
- የባህሪ ለዉጥ ፕሮግራሞች (የአቻ ለአቻ፤ የህይወት ክህሎት፤ ወዘተ)
- የኮንዶም አቅርቦትና ስርጭት
- የአልኮል እና ሌሎች ዕፆችን ተጽዕኖአቸውን መቀነስ እና ማስወገድ

II. የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሕክምና አገልግሎቶች (Bio-medical services)

- የኤች.አይ.ቪ ምክርና ምርመራ አገልግሎት፣
- የፀረ-ኤችአይ ቪ መድኃኒቶች ሕክምና አገልግሎት፣
- ኤች.አይ.ቪ ከእናት ወደ ልጅ/ጽንስ እንዳይተላለፍ ህክምና አገልግሎት ፣
- ከኤች.አይ.ቪ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው በሽታዎች ሕክምና (የቲቢ፤ የአባላዘርና ቫይራል ሄፓታይተስ በሽታዎች ህክምና)፣

III. መዋቅራዊ ፕሮግራሞች (Structural intervention) ፡-

- ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከል አዎንታዊ አስተዋፆ ሊያበረክቱ የሚችሉ አሰራሮችና ህጎችን ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም አሉታዊ አስተዋፆ ያላቸዉን ማስተካኪያ እንዲደረግባቸዉ ማድረግ፡፡
- የኤች.አይ.ቪ ምክርና ምርመራ አገልግሎት (HIV Testing & Counseling)
- የኤች.አይ.ቪ የምክክርና ምርመራ አገልግሎት (HCT) ዓይነቶች

1. በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የኤች.አይ.ቪ ምክክር እና ምርመራ አገልግሎት /VCT/
2. በጤና ባለሙያ አነሳሽነት የሚከናወን የኤች. አይ.ቪ ምርመራና ምክክር አገልግሎት (PITC)
3. ኤች.አይ.ቪ እራስን በራስ መመርመር (HIV self-test)

ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አገልግሎቶች ተደራሽነት ተግዳሮት የሚሆኑ ምክንያቶች

2. የፀረ-ኤች.አይ.ቪ ሕክምና አገልግሎት

አንድ ሰው ተመርምሮ ኤች.አይ.ቪ በደሙ ውስጥ ከተገኘ በጤና ባለሙያ ትዕዛዝ መሠረት ወዲያውኑ የፀረ-ኤች.አይ.ቪ መድሃኒት ይጀምራል፤የፀረ-ኤች.አይ.ቪ መድሃኒት በጤና ባለሙያ በታዘዘዉ መሰረት በአግባቡ የሚወሰድ ከሆነ የሚከተሉት ጥቅሞችን ያገኛል፤የኤች. አይ.ቪ ቫይረስ መጠን እንዲቀንስ (ኤች.አይ.ቪ ቫይረስ በሰዉነት ዉስጥ እንዳይባዛ ይረዳል)፤የሰውነታችን የበሽታ መከላከያ ሲዲ 4 መጠን እንዲጨምር ይረዳል፤ የተጓዳኝ በሽታዎችን እና ሞትን ለመከላከልና ለመቀነስ ያግዛል፤ጤናማ ሕይወት ለመኖር ያግዛል፤ኤች.አይ.ቪ ወደ ሌላ ሰዉ መተላለፍን ይገታል እንዲሁም ለቫይረሱ ስርጭት መቀነስ ትልቅ አስተዋፆ ያበረክታል፤የአድሎና መገለልን ፍራቻ ብዙ ሰዎች የፀረ-ኤች.ኤ.ቪ ህክምና አይከታተሉም፤

ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አገልግሎቶች ተደራሽነት ተግዳሮት የሚሆኑ ምክንያቶች

ኤች.አይ.ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል ፕሮግራም (Pmtct)

- ኤች.አይ.ቪ ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍን ሙሉ በሙሉ ለማስቀረት እናቶች የቅድመ ወሊድ አገልግሎት፣የወሊድ አገልግሎት እና የፀረ-ኤች.አይ.ቪ መድሃኒትን በአግባቡ መከታተል እንዲሁም ጡት በማጥባት ወቅት የጤና ባለሞያ ምክር በመከተል እና ተያያዥ የህክምና አገልግሎቶችን በመጠቀም ከቫይረሱ ነፃ የሆነ ልጅ ወልዶ ማሳደግ ይቻላል፡፡
- ከሌላዉ ፕሮግራም አፈፃፀም አናሳ መሆን የሚጠቀሰዉ ምክንያት የባሎች ተሳትፎ አናሳ መሆኑ ነዉ፡፡ በ2014 ዓ.ም ምርመራ ከመጡ ነፍሰጡር እናቶች የትዳር አጋራቸዉ አብሯቸዉ ለምርመራ ወደ ጤና ተቋም የመጡ ባሎች 24% ብቻ ናቸዉ፡፡ ከኤች.አይ.ቪ ነፃ ትዉልድ ለማፍራት የባሎችም ተሳትፎ ትልቅ አስተዋፆ አለዉ፡፡

ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አገልግሎቶች ተደራሽነት ተግዳሮት የሚሆኑ ምክንያቶች

. የአባላዘር በሽታ ምርመራ እና ህክምና አገልግሎት

- የአባላዘር በሽታ ምልክቶች በታየ ጊዜ በወቅቱ ምርመራ በማድረግ ህክምና ካልተደረገ በኤች.አይ.ቪ የመያዝን እድል በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል፡፡
- የአባላዘር በሽታ ምልክቶች በታየ ጊዜ በአፋጣኝ እራሶን እና ፍቅረኛዎትን/የትዳር አጋሮን/ የወሲብ ተጓዳኞትን ህክምና ማስጀመር ያስፈልጋል፡፡
- በ2014ዓ.ም ለዓባላዘር ህክምና ወደ ጤና ተቋም መጥቶ ህክምና መዉሰድ ካለባቸዉ ሰዎች 43% ያህል ብቻ ነዉ ህምናዉን የወሰዱት፡
- የአባላዘር ህክምና ሽፋን በሚፈለገዉ መጠን ከፍ እንዳይል ከሚያደርጉት ምክንያቶች አንዱ እና ዋነኛዉ በማህበረሰባችን ዉስጥ ስለ አባላዘር በሽታ ያለዉ የተሳሳተ አመለካከት ነዉ፡፡
- በማህበረሰባች ዉስጥ ያለዉን የተሳሳተ አመለካከት በማስተካከል የበሽታዉ ምልክት የታየባቸዉ ሰዎች ከልማዳዊ አመለካከት ይልቅ በአፋጣኝ ወደ ጤና ተቋም በመሄድ ህክምናዉን በመከታተል መዳን እንደሚቻል በማሳወቅ የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን ማሳደግ ይጠበቃል፡፡

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከል እና በመቆጣጠር ረገድ የባለድርሻ አካላት ሚና

አጠቃላይ ማህበረሰቡ

የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አገልግሎቶች ተደራሽነታቸዉን ማረጋገጥ (በተለይ ለይበልጥ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች)፣ወጣቶችን (በት/ቤት እና ከት/ቤት ዉጭ ያሉ) ለኤች.አይ.ቪ አጋላጭ ከሆኑ ባህሪ እንዲታቀቡ እና አዎንታዊ ባህሪ እንዲያዳብሩ ማገዝ፣አድሎ እና መገለልን ማስቀረት (በማህበራዊ ህይወት፤ በስራ ቦታ፤ ወዘተ)፣ኤች.አይ.ቪ በደማቸዉ ያለባቸዉ ወገኖች አስፈላጊዉን እገዛ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

በየደረጃዉ ያለ አመራር

ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭት መንስዔዉ ዘርፈ ብዙ እንደመሆኑ እና የሚያስከትለዉም ተፅዕኖ ብዙ ከመሆኑ አንፃር ፤ ቫይረሱን ለመከላከል የሚደረገዉ ጥረትም ዘርፈ ብዙ መሆን ይኖርበታል፡፡ በየደረጃዉ ያለ አመራርም ይህን ከግንዛቤ በማስገባት ለዘርፈ ብዙ ኤች.አይ.ቪ ምላሽ አስፈላጊዉን ትኩረት መስጠት፤ በቂ በጀት መመደብ እና የፕሮግራሞችን ተፈፃሚነት ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

የሲቪክ ማህበራት

ለኤች.አይ.ቪ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን ትኩረት በመስጠት የኤች.አይ.ቪ ፕሮግራሞችን ተደራሽ ማድረግ፣የአድሎ እና መገለልን ለማስቀረት ማህበረሰቡን ማስተማር ፣ወጣቶች ከኤች.አይ.ቪ እራሳቸዉን እንዲከላከሉ ማብቃት ከሲቪክ ማህበራት የሚጠበቁ ሃላፊነቶች ወይም ሚናዎች ናቸው፡፡

የጤና ባለሞያዎች

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አገልግሎቶችን ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ያለምንም አድሎ መስጠት፣ ለኤች. አይ.ቪ ይበልጥ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን ትኩረት አድርጎ የመከላከል አገልግሎት መስጠት የሚጠበቁ ሚናዎች ናቸው፡፡

## የ18ኛው. . .

ከገጽ 1 የዞረ

ለጋራ እድገትና ስኬት እንዲሁም ለሀገረ መንግስት ግንባታችን ወሳኝ ሚና ስላለው ሁሉም ባለድርሻ አካላት በዚህ ረገድ ርብርብ ማድረግ ይጠበቅብናል በማለት የእንኳን ደህና መጣችሁ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

የኢኮኖሚ ልማትና ፕላን ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ኃ/ማርያም ዳዲ የሲምፖዚየሙን የመወያያ ሰነድ ያቀረቡ ሲሆን የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት ም/አፈ ጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ከሪማ አሊና የሀረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አፈ ጉባኤ የተከበሩ አቶ ሱልጣን አብዱሰላም የውይይት መድረኩን መርተዋል።

በዚህም በድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት አስተባባሪነት ሲከበር የነበረው 18ኛው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በአል የተጠናቀቀ ሲሆን እንደሀገር አቀፍ ከህዳር 25 እስከ 29 በጅግጅጋ ከተማ እንደሚከበር ተገልጿል ሲል የአስተዳደሩ ምክር ቤት ህዝብ ግንኙነት ዘግቧል፡፡

# ድሬና... . "ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ"

በኤደን ሳሙኤል

የተሟላ መሰረተ-ልማትና ለዛም የሚሆን አስቻይ አቅም መገንባት ለሃገሪቱ የዲጂታል ምህዳር መስፋፋትና ለአጠቃላይ የምጣኔ ሃብት እድገት ወሳኝ መሆኑ እሙን ነው። የቴሌኮም ፣ የኤሌክትሪክና የመንገድ አገልግሎቶች ተደራሽ መሆን እና የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን በቅርበት ማግኘት ዜጎች በዙሪያቸው ካለው ከባቢ ጋር በቀላሉ እንዲገናኙና ሁኔታዎችን እንዲረዱ ያደርጋል።

ፈጣን የግንኙነት ምህዳርና ለዛም አማራጮች መኖራቸው ግለሰቦችን ለመረጃ ይበልጥ ቅርብ ያደርጋል ፣ ክህሎቶችን ለመፍጠርና ለማሳደግ እድሎችን ይፈጥራል፤ እንዲሁም ገቢንና የፈጠራ ችሎታን ለማሳደግ በተጨባጭ ይረዳል። የበይነ-መረብ ተጠቃሚነት መጨመር ከሃገራት ምጣኔ-ሃብታዊ እድገት መፋጠንና የጥቅል አመታዊ ገቢ እድገት ጋር አዎንታዊ ትስስር ሊኖረው እንደሚችል ማሳያዎች አሉ።

ታዲያ በአገራችን ለበርካታ አመታት የተግባቦቱን (የኮሙኒኬሽኑን) ዘርፍ በብቸኝነት ሲሰራበት የነበረው ኢትዮ ቴሌኮም ለሀገራችን ዲጂታላይዜሽን እድገት ከፍተኛውን ሚና እንደተወጣ እርግጥ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የቴሌኮም የኔትዎርክ ሽፋን ባለፉት አመታት ከፍተኛ መሻሻል አሳይቷል። በመንግስት ባለቤትነት የተያዘውና የሃገሪቱ ግዙፍ የቴሌኮም አገልግሎት ሰጪ የሆነው "ኢትዮ-ቴሌኮም" የአገልግሎት ሽፋኑ ከሃገሪቱ መልክአ-ምድር 85 በመቶ ያህል መድረሱን ይገልፃል።

ታዲያ ድሬዳዋ እና ነዋሪዎቿም አስተማማኝ የሚባል የቴሌኮም አገልግሎት ያገኛሉ። የቴሌኮም አገልግሎት በከተማዋ ለሚደረጉ የዕለት ተእለት እንቅስቃሴዎች በተለይም ለንግድ እና ማህበራዊ ግንኙነቶች በጣም መሰረታዊ ነው።

የኢትዮ-ቴሌኮም ከፍተኛና ሁሉን አቀፍ የኮሙኒኬሽን ስራ በድሬ የበይነ-መረብ አገልግሎት ላይም በስፋት ጥቅም ላይ ውሏል። ኢትዮ ቴሌኮም የቤት ለቤት ብሮድባንድ ኢንተርኔት" አገልግሎት ላይ የዋጋ ቅናሽ ማድረግ ስትራቴጂ መከተሉ እንደ አዲስ አበባ ሁሉ በድሬዳዋም የአገልግሎቱን ፈላጊዎችና ተጠቃሚዎች ቁጥር ከፍ አድርጎታል።

ምንም እንኳን በክልሎችና በከተሞች ተደራሽነት ተተንትኖ የተገለፀ አሃዛዊ መረጃ ባይቀመጥም ኢትዮቴሌኮም የመደበኛ ብሮድባንድ ኢንተርኔት አገልግሎቱ ተጠቃሚዎችን ቁጥር በ765% በማሳደግ ባለፉት አራት አመታት ብቻ የአገልግሎቱ ደንበኞች ግማሽ ሚሊዮን እንደደረሱ ይፋ አድርጓል።

ይኸው መንግስታዊው የቴሌኮም አገልግሎት ሰጪ ተቋም በግንቦት ወር 2013 ዓ.ም በድሬዳዋ ከተማ የአራተኛው ትውልድ "4G" ኢንተርኔት አገልግሎት አስጀምሯል። እስከ 2015 ዓ.ም ባለው መረጃ የድሬዳዋ ከተማን ጨምሮ ኢትዮቴሌኮም በምስራቅ ኢትዮጵያ ዲስትሪክት 1.6 ሚሊዮን ደንበኞች የተለያዩ አገልግሎቶቹን ይጠቀማሉ። የፌስቡክ (ሜታ) ማስታወቂያ መተግበሪያን መሰረት ተደርጎ በተወሰደ ግምታዊ አሃዝ በድሬዳዋ እስከ 150,000 የሚሆኑ የፌስቡክ ተጠቃሚዎች እንዳሉ ይታሰባል።

በቅርቡ በኢትዮጵያ የቴሌኮም ዘርፍ የመጀመሪያው የግል አገልግሎት ሰጪ ኩባንያ በመሆን ዘርፉን የተቀላለቀው "ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ" ከወራቶች (እንደውም አንድ አመትን ለማስቆጠር በሂደት ላይ ነው) በፊት የሙከራ አገልግሎቱን ሲጀምር ድሬዳዋን የመጀመሪያዋ ከተማ አድርጎ መርጧታል። የድሬዳዋ ከተማ ነዋሪዎች በሳፋሪኮም አማራጭ አገልግሎት ማግኘታቸውን በደስታ እንደተቀበሉት የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡

የሙከራ አገልግሎቱ በይፋ ሲጀምርም በሺዎች የሚቆጠሩ ነዋሪዎች ከሳፋሪኮም መደብሮች ሲም ካርድ ለመግዛት ሰልፍ ይዘው ውለው ማደራቸውም ይታወሳል፡፡ በርካታ የድሬዳዋ ነዋሪዎች ዘመናዊ የስማርት ስልክ ተጠቃሚዎች በመሆናቸው (አንጻራዊ ሲታይ) የቴሌኮም አገልግሎት ኔትወርኩን ከማስጀመር ባሻገር በተመጣጣኝ ዋጋ የሞባይል ቀፎዎችን አብሮ በማቅረብ ስራውን የጀመረው የሳፋሪኮም መግባት ደግሞ የስማርት ስልክ ተጠቃሚዎችን ቁጥር ይበልጥ እንደጨመረው የአደባባይ




ላይ ሀቅ ነው።

በነገራች ላይ ውድ አንባቢያን እዚህ ጋር ስለ ሳፋሪኮም ኢትዮጲያ ካነሳን አይቀር ስለተቋሙ አንዳንድ መረጃዎችን ላቀብላችሁ እና ተቋሙ ለከተማችን ወጣቶች የፈጠረውን የስራ እድል እንዳስሳለን፡፡ በግንቦት ወር 2013 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የቴሌኮም ፈቃድ አግኝቶ ወደ ገበያው የገባው የኬኒያው ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ስራ ለመጀመር የሚያስችለውን የመጀመሪያ ዙር የኔትዎርክ ዝርጋታና የመረጃ ቋት ግንባታ አጠናቆ ወደ ስራ ከገባ አንድ አመት ሊቆጠር ነው፡፡

ሳፋሪኮም አገልግሎቱን በ07 የመነሻ ቁጥር የሚያቀርብ ሲሆን የድምጽ፣ የአጭር መልእክት፣ የቪዲዮ ጥሪ እንዲሁም የዳታ አገልግሎቶቹን ይሰጣል፡፡ መሰረተ ልማቶች ከኢትዮ ቴሌኮም በመከራየት እንዲሁም የራሱን በመገንባት ስራውን የጀመረው ኩባንያው የኢትዮ ቴሌኮምን የቴሌኮሙንኬሽን መሰረተ ልማቶች ለመጠቀም የሚያስችል ድርድር መጀመሩን በድርጅቱ ከፍተኛ የቴክኖሎጂ አፊሰሩ ፔድሮ ራባካል ኩባንያው በተቋቋመበት ወቅት ለአዲስ ቲቪ በሰጡት ቃለ-ምልልስ ወቅት ታውቋል፡፡

እስካሁን ለመሰረተ ልማት ግንባታና ለቁሳቁስ ግዥ ከ300 ሚሊዮን ዶላር በላይ ያወጣው ሳፋሪኮም በቀጣይ አስር ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያ 8.5 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር መዋዕለ ነዋይ ኢንቨስት ያደርጋል ተብሎም ይጠበቃል፡፡

የታዋቂው የቴሌኮም ኩባንያ ቮዳኮም ቤተሰብ የሆነው ሳፋሪኮም ከሚሰጠው መደበኛ የቴሌኮም አገልግሎቶች በተጨማሪ በተከታታይ በሀገሪቱ የዲጂታል ዘርፍ የጎላ ሚና ይኖራቸዋል የተባለላቸውን በፋይናንስ፣ በትምህርት፣ በጤና በግብርና፣ እንዲሁም በሌሎች ዘርፎች በርካታ አገልግሎቶችን ለመስጠት ማቀዱ የድርጅቱ ከፍተኛ የቴክኖሎጂ አፊሰሩ ፔድሮ ራባካል ተናግረዋል።

ኩባንያኛው በአሁኑ ሰዓት 800 ኢትዮጵያውያንን ቀጥሮ እያሰራ የሚገኝ ሲሆን በዓመቱ መጨረሻ ከ1,000 በላይ የሚሆኑ አዳዲስ ሰራተኞች ኩባንያውን ይቀላቀላሉ ተብሏል። በተመሳሳይ ሳፋሪኮም በኢትዮጵያ ይፈጥራቸዋል በተባሉ የተለያዩ የዘርፉ ዕድሎች በቀጣይ 10 ዓመታት ውስጥ ለ1.6 ሚሊየን ሰዎች የስራ እድል ይፈጥራል ተብሎ ይጠበቃል።

ሳፋሪኮም ከሳይበር ደህንነት አንጻር ምን ያህል አስተማማኝ ቴክኖሎጂ ይጠቀማል ተብሎ ከጋዜጠኞች ለቀረበላቸው ጥያቄ ፔድሮ ሲያብራሩ በዓለም ላይ በአሁኑ ሰዓት አለ የተባለውን አስተማማኝ የዲጂታል ሴኩሪቲ ሲስተም እንደሚጠቀምና ይህም የደንበኞችንም ሆነ አጠቃላይ የተቋሙን መረጃዎች በአስተማማኝ መልኩ ለመያዝ እንደሚያስችለው ገልጸዋል።

በሌላ በኩል ደንበኞች ከአንዱ የቴሌኮም ድርጅት ደንበኝነት ወደ ሌላኛው መቀየር የሚችሉበትን ቴክኖሎጂ የመተግበር የረጅም ጊዜ ዕቅድ እንዳለው ተገልጿል። የቴክኖሎጂው አቅም ሲፈቅድ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመነጋገርና የሚከወን ይሆናል ተብሏል።

አሁን ላይ ባለው የኃይል፣ የደህንነት እንዲሁም የማቀዝቀዣ አቅም አንጻር ታየር 3 የተባለውን የመረጃ ቋት ደረጃ በጠበቀ መልኩ መገንባቱን የገለጹት የቴክኖሎጂ አፊሰሩ በመረጃ ቋቱ ግንባታም ሆነ በሌሎች የተቋሙ የኔትወርክ ዝርጋታ ላይ በመላው ዓለም የሚገኙ ከ200 በላይ የቴክኖሎጂ መሀንዲሶች በቀጥታ እየተሳተፉ እንደሚገኝና ሳፋሪኮም ወደፊት አገልግሎቱን ዘመኑ በሚፈልገው ደረጃ በፍጥነት እያሳደገ እንደሚሄድ ገልጸዋል።

የቴሌኮም ተቋሙ በቀጣይ ዓመታት በደንበኞቹ ፍላጎት ላይ በመመስረት በርካታ የቴሌኮም አገልግሎቶችን ለደንበኞች የሚያቀርብ ሲሆን ለዚህም እንደ አፕል፣ ጎግል፣ ሳምሰንግ ከተሰኙትና ሌሎችም ዓለም አቀፍ የቴክኖሎጂ ተቋማት እንዲሁም ከኢትዮጵያውያን ተቋማትና ባለሙያዎች ጋር በመሆን እሰራለሁ ብሏል።

በፈረንጆቹ 2023 ዓ.ም. 25 ከመቶ የሚሆነውን የሀገሪቱን ህዝብ ለማዳረስ ዕቅድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ የሚገኘው ሳፋሪኮም በአሁኑ ሰዓት በአዲስ አበባና በአዳማ የገነባቸው የመረጃ ቋቶች እያንዳንዳቸው እስከ 10 ሚሊየን ደንበኞችን የማስተናገድ አቅም ያላቸው ሲሆን ኩባንያው በቀጣይ ተመሳሳይ ማዕከላትን በዘጠኝ ከተሞች እንደሚተክል ታውቋል።

ዋና መሥሪያ ቤቱ ናይሮቢ የሚገኘው ሳፋሪኮም የኬንያ የቴሌኮም ድርጅት ሲሆን፤ ኬንያ ውስጥ ትልቁ የቴሌኮም አገልግሎት አቅራቢና በምሥራቅ እና በመካከለኛው አፍሪካ ትርፋማ ከሆኑ ድርጅቶች መካከል አንዱ ነው። ታዲያ መስሪያ ቤቱ በከተማችን ድሬደዋም ቅርንጫፎቹን በመክፈት ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል በመፍጠር የኑሮ አለኝታ ሆኗል፡፡

ለ2 አመታት በማሪያም ሰፈር ት/ቤት በመምህርነት ያገለገለው ወጣት እዮናዳብ ቁምነገር የሳቢያን ሰፈር በተለምዶው መስቀለኛ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ ነው፡፡ ትውልዱና እድገቱም እዚሁ ድሬደዋ ከተማ የሆነው ወጣቱ አሁን ላይ በሳፋሪኮም ኢትዮጲያ መስቀለኛ ቅርንጫፍ የሽያጭ ባለሞያ በመሆን ተቀጥሮ እየሰራ ይገኛል፡፡ ወጣቱ ባለትዳርና የአንድ ልጅ አባት ሲሆን እናትና አባቱን የመንከባከብ ሀላፊነቱም የሱ እንደሆነ ነግሮናል፡፡

« ከመምህርነት ስራ ለቅቄ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደዚህ ስቀላቀል አንዳንድ መደነጋገሮች ነበሩ፡፡ ኩባንያው አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሲም ካርድ ሽያጭ ስራን በጀመርንበት ወቅት ከበርካታ ደንበኞች ጥያቄዎች በስፋት ይቀርቡ ነበረ፡፡ እንዲሁም ደግሞ ሲም ካርዱ በአንድ ጊዜ በድሬዳዋ ከተማ ነዋሪዎች ዘንድ ተቀባይ ስለነበረ የስራ መደራረብ ጫናዎች ነበሩ፡፡ ነገር ግን ከጊዜ ብዛት ስራውን ለምጄዋለሁ። ሳፋሪኮም ኢትዮጲያ ድሬዳዋ ላይ ቅርንጫፍ መክፈቱ ለመስተዳደሩ ወጣቶች በርካታ ጥቅምን ይሰጣል ብሎናል፡፡

አሁን ላይ አብዛኞቹ የድሬዳዋ ልጆች ከዩኒቨርስቲ ከተመረቁ በኋላ ስራ ማግኘት ስለሚከብዳቸው አልባሌ ቦታዎች ላይ እየዋሉ ነው፡፡ በዚህም እንደነዚህ አይነት ዘመናዊ ኩባንያዎች በከተማዋ ላይ ኢንቨስት ሲያደርጉ ደግሞ የወጣት ሙሩቃን ስራ አጥ ቁጥሩን በከፍተኛ ደረጃ ይቀነሰዋል» በማለት ወጣቱ ሀሳቡን ያጋራል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በዛው የሳፋሪኮም ቅርንጫፍ በጥበቃ ሰራተኝነት ስትሰራ ያገኘናት ወ/ሮ ሂሩት ማስረሻ ይህንን ስራ ባላገኝ ኖሮ ልጆቼን ማስተማር አልችልም ነበር ትላለች፡፡ ወ/ሮ ሂሩት የገንደተስፋ ሰፈር ነዋሪ ስትሆን የ2 ልጆች እናት ናት ፡፡ ከዚህ ቀደም የተለያዩ የንግድ ስራዎችን ሞክሬ ነበረ፡፡ ነገር ግን የንግዱን ሁኔታ በአግባቡ ሳላጠና ስራ ውስጥ በመግባቴ ለኪሳራ ተዳርጌ ነበረ። ከዛም ከሀገሬ ተሰድጄ ወደ አረብ ሀገር በቤት ሰራተኝነት ለመስራት ሄጄ ነገር ግን በህገወጥ መንገድ ከሀገር ስለወጣሁ ተይዤ ካለምንም ክፍያ ወደሀገሬ መጣሁ ትላለች፡፡ በዚህ በጣም ተጎድቼ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ እያለሁ ይንንን የስራ እድል ተወዳድሬ በማግኘቴ ደስተኛ ነኝም ትላለች፡፡

ወይዘሮዋ አያይዛም ስራውን ስጀምር ከበርካቶች ዘንድ ትችቶች ተሰንዝረውብኝ ነበረ እሱንም ተቋቋሜ ዛሬ ላይ በመድረሴ በማገኘው ገቢ ልጆቼን አስተምራለሁ ትላለች፡፡ ሳፋሪኮም ኢትዮጲያን በድሬዳዋ ለሚገኙ በርካታ ወጣቶች እንዲሁም በሁሉም እድሜ ክልል ለሚገኙ ነዋሪዎች በየዘርፉ ስራ በመፍጠሩ ደስተኛ መሆኗን ገልፃለች፡፡ በቀጣይም በተለይም ወጣት ሴቶች ስራን ሳይንቁ በመስራት ራሳቸውን ብሎም ቤተሰባቸውን እንዲረዱ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በመጨረሻም ውድ አንባቢያን ኩባንያው አሁን ላይ የግንኙነት አድማሱን በማስፋት ላይ ሲሆን በዚህም በቅርቡ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የዲጂታል አሰራሮችን ለማስፋትና ለማጠናከር የሚያስችለውን የመግባቢያ ሥምምነት ተፈራርሟል፡፡ ሥምምነቱን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዝዳንት አቤ ሳኖና የሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስኪያጅ አንዋር ሶሳ የፈረሙት ሲሆን በዚህም በርካቶች ይጠቀማሉ ተብሎ ይጠበቃል።

የባንኩ ፕሬዝዳት አቶ አቤ ሳኖ በፊርማው ስነስርአት ወቅት እንደገለፁት ባንኩ የደንበኞችን ፍላጎት ለማርካት የተለያዩ ዘመናዊ አሰራሮችን ተግባራዊ እያደረገ ነው። የባንኩ ተቀማጭ ገንዘብ ከአንድ ትሪሊየን መሻገሩን ገልጸው፤ ለዚህም የዲጂታል አገልግሎት መስጠት መጀመሩ ለስኬቱ የጎላ አስተዋጽዖ አበርክቷል። አሁንም የተለያዩ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጡን ይበልጥ ለማዘመን በትኩረት እየሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

በመሆኑም በዚህ ስራ ላይ ደግሞ ሳፋሪኮም ሲታከልበት በባንኩ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች በዘመናዊ አሰራር የተደገፉ ለማድረግ እንደሚያግዝ ነው የተናገሩት። ይህም የባንኩን አቅም ከማሳደግ በዘለለ የተገልጋዩንና የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማድረስ እንደሚረዳ አብራርተዋል። የሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስኪያጅ አንዋር ሶሳ በበኩላቸው በኢትዮጵያ የዲጂታል ተደራሽነት እየተስፋፋ መምጣቱ የሚበረታታ ነው። በተለይም "ዓለማችን በልዩ ልዩ የቴክኖሎጂ ሥራዎች አንድ እየሆነች በመጣችበት በዚህ ጊዜ አማራጮችን በማስፋት ተደራሽ ማድረግ የግድ ያስፈልጋል" ብለዋል። በተለይም ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች በዲጂታል አሰራር መደገፋቸው ዘመናዊነትን ከማጉላት በዘለለ አገራዊ ፋይዳውም የጎላ ነውም ሲሉ ተናግረዋል፡፡

# ሸበላው

## ከባለፈው ሳምንት የቀጠለ

በአዜብ ሽፈራው /አዚዛ/

ሐይማኖት የእየሩስን ነገር ማብሰልሰል ጀመረች፡፡ ሳሚ ፍቅረኛዬ መስሏት ነው ትገርማለች በማለት ለብቻዋ ከመስታወት ጋር ማውራት ጀመረች ጥሩ ገምታለች፡፡ አንድ ቀን የእኔ መሆኑ አይቀርም ወይኔ ደስ የሚል ስሜት አለው በቃ ሳሚን አፈቀርኩት ማለት ነው? እሱ እግዚአብሔር ሁሉን አሟልቶ ሰጥቶታል ልክ እንደ መልአክ መልክ፣ቁመና ጥሩ ፀባይ፣ ለሰው ያለው አክብሮት፣ እኔን እንኳን ቀርቦ የፍቅሩ ምርኮኛ አደረገኝ እኮ! የእኔ ጀግና ተማረኩልህ፤ የልቤ ንጉስ የእየሩስን ነገር እኔ ጨርሰዋለሁ፤ ይሄ ጣልቃ የምትገባው ነገሯን ታቆማለች፤ እሱ ብቻ እንደሚወደኝ ላረጋግጥ እንጂ ሌላው ቀላል ነው አለች፡፡

ሐይማኖት ወደለመደችበት መዝናኛ በሰዓቷ ሄደች ሳሚ አላያትም ነበር፡፡ እየሩስ ግን ከፉኛ ትገላምጣት ጀመር፡፡ እሷም ወደ መታጠቢያ እንደመግባት ብላ እየሩስን በአይኗ ምልክት ሰጠቻት፡፡ ተከታትለው ገቡ ሐይማኖት ቆይ አንቺ ከእኔ ምን ፈልገሽ ነው? ሳሚን እሱ ምንሽ ነው? እስካሁን ምኔም አልነበረም፡፡ ከዚህ በኋላ የእኔ ይሆናል፡፡ እንደዚህ ከሆነ ከተኛሽበት ንቂ እየቃዠሽ ነው! እሱ መቼም ያንቺ አይሆንም የእኔ ብቻ ነው እናት እና እህቱ እንኳን ከእኔ ሊወስዱብኝ አይችሉም፡፡ እንኳን ላፈቀርኩት ላመንኩበት ነገር እስከጥግ የምራመድ ጀግና ነኝ የእኔ መሆን የማይችል ከሆነ የማንም አይሆንም፡፡

ተነጋግረው ሲጨርሱ ተከታትለው ወጡ፡፡ ሃይ ሐይሚ ከየት ነው እዚህ ነበርሽ እንዴ? አዎ ስራ ላይ ስለነበርክ እንዳልረብሽህ ነበር ዝም ያልኩህ፡፡ እዘዥኝ አዎ ወይን ከመቼ ወዲ ሐይሚ ፍቅር ከያዘኝ ጀምሮ ማነውሱ ባክሽ? እኔና ልቤ እናውቀዋለን እሱ ግን አያውቅም፡፡ ይከብዳል በጣም ለምን አትነግሪውም? አንድ ቀን እነግረዋለሁ፤ አዝኛለሁ ተቀድሜአለኋ?አትዘን እኔ የማንም አይደለሁም ይልቅ አንተ ሳትያዝ አይቀርም? በአንቺ ነዋ! አትቀልድ! ታዲያ ማን ናት አገኘሽልኝ? እሷ አገኘችህ እንጂ! አሁንም እንዳትቆጣህ ተነስ ወደ እሷ በማላውቀው ነገር እንዳልጎዳ እዩ ናት? እሷ አሁን ከአንተ ጋር ስትመለከተኝ ነው የታወቃት እስከ ዛሬ ከስራዋ በስተቀር አስባኝ አታውቅም እንኳን እኔን በፍቅሯ የሚንገበገብላትን ይሳቆርን እምቢ ብላው እየተሰቃየ ነው አሁን አንቺን ስታይ ማበድ ጀመረች፡፡

ወደ እየሩስ ተራመደና እዩ ምን ነክቶሽ ነው? ከልጅቷ ምንድነው የምትፈልጊው? ትልቁ ነገር አንተን! ይሄ ደግሞ ምን ማለት ነው? ገብቶሃል! ለማንኛውም አስጠንቅቃኛለች፡፡ ግን እኔ የእሷን ማስጠንቀቂያ አልቀበልም ምክንያቱም አንተ የእኔ ትሆናለህ ከመቼ ወዲህ ነው እንደዚህ አይነት ሀሳብ ያመጣሽው አትጠይቀኝ አንተ መነኩሴ ይመስል አንዴ እንኳን ከሴት ጋር ስትወጣ አላየሁህም ስትመኝም ጭምር ታዲያ በምን አይነት መልኩ ልቅረብህ አንቺ ግን እኔ ከይሳቆር በምን ተለይቼ ነው እንደዚህ የወደድሽኝ ከእኔ ጋር እልህ ውስጥ የምትገቢው ከእኔ ራቂ ወደ ራስሽ ተመለሺ ከአንተ መራቅ እንደማልችል ስንቴ ልንገርህ? አንተ ቦታህ ከእኔ ጋር ነው አትሳሳቺ መቼም እሱ አይሆንም አትድከሚ፡፡

እየሩስ ሳሚ በሐሳቧ ስላልተስማማ በመዝናኛው አጠገብ ካሉት የጎዳና ልጆች መካከል ከሳንቾ ጋር በጣም ትግባባ ነበርና ጠርታ አዋራችው፡፡ እሱም በሀሳቧ ተስማማ ሳሚ ከስራ ሲወጣ ጠብቀው ከኋላው በማፈን እራሱን እንዲስት ካደረጉት በኋላ በአንድ ባዶ መጋዘን ውስጥ አሰሩት ሳንቾዬ እንዳትጎዱት ዝም ብላችሁ ከወንበር ጋር እሰሩት እጁን እንዳይሰበር ተጠንቀቁ! በቃ እዬዬ አትበይብኝ ምን ገተታ ታበዛብናለች እንዳንለቀው እሺ በቃ እሄዳለውኝ፡፡ ሳሚ ሲነቃ መጋዘን ውስጥ ከወንበር ጋር ተጠፍንጎ እራሱን አገኘ፡፡ እናንተ እነማን ናችሁ? ከእኔ ምንድነው ምትፈልጉት? እኛ ከአንተ ምንም አንፈልግም አንተን የሚፈልጉ ግን ብዙ ናቸው፡፡ ታዲያ ልብ ካላቸው ለምን ፊት ለፊት አይገጥሙኝም? እሱን ሲመጡ ጠይቃቸው እኛ ስራችንን እየሰራን ነው፡፡

እየሩስ ደወለላትና መጣች፡፡ ቀና ብሎ አያትና እንዴ አጅሪት በእንደዚህ አይነት ፍቅር የሚገኝ መስሎሽ ከሆነ ተሳስተሸል፡፡ ታዲያ ምርጫ አልሰጠኸኝም እኮ ምን ላድርግ ሳሚ? የበለጠ ጠላሁሽ በዚህ መልኩ ልታሳምኚኝ ካሰብሽ ተሳስተሸል፡፡ ግን አንቺ ጤነኛ አትመስይኝም፤ አዎ እብድ ነኝ በአንተ ምክንያት አብጃለሁ! ሐኪሜ አንተ ነህ በሽታዬም አንተ ነህ! ካልሆነ አንተ የማንም ስትሆን ማየት አልችልም፤ ተያይዘን እናልቃለን፡፡ አየሽ አንቺ ፍቅር ምን እንደሆነ አታውቂም፡፡ ፍቅር ባፈቀሩት ሰው ደስታ መደሰት እንጂ ስቃዩን መመልከት አይደለም፡፡ እኔ አንቺን ፈርቼሽ እንኳን ብሆን በድኔን እንጂ ፍቅሬን አታገኚም፡፡ እኔ ልቤን ለሌላ ሰጥቻለሁ! እኮ ለዚያች? በፍፁም ሳሚዬ አይሆንም፡፡ አንተ ለእኔ ነው የምትገባው፤ ከእኔ ጋር ነው የምንተዋወቀው፤ እሷን እኮ ያወካት አሁን በቅርቡ ነው፡፡ ሳሚ አፈቅርሃለሁኝ!! ሳንቾ ምግብ ስጡት ውሃም አጠጡት፡፡

በማግስቱ ጠዋት ሳሚ ስራ አልገባም ነበር፡፡ የቤቱ ባለቤት አቶ ታደሰ ሲገባ አላገኘውም፡፡ ሳሚስ የታለ አልገባም? የት ሄዶ ነው አርፍዶ አያውቅም፡፡ ለማንኛውም ሲመጣ ወደ እኔ ላኩት አልመጣም ነበር? አሁንም ታዴ ተመልሶ ጠየቀ፡፡ አልመጣም እስቲ ደውሉለት፤ ስልኩ ይጠራል አይነሳም! ማታ ሰዓት ነው የወጣው ሰባት ሰዓት ቤተሰብ ጋር ደውሎ ሄሎ ሳሚ ምን ሆኖ ነው ስራ ያልገባው? ኸረ ትላንት ለስራ እንደወጣ ነው፡፡ ሳሮን ወደ እየሩስ ጠጋ አለችና እዩ ሳሚን አይተሽዋል ? አላየሁትም! እዩ እውነቱን ንገሪኝ? እኔ ሳሚን ጠባቂ ነኝ? ብላ ድምጿን ከፍ አድርጋ መጮህ ጀመረች፡፡ ቤት ውስጥ ያሉ ሰዎች ደነገጡ ሁሉም ትኩረታቸውን እሷ ላይ አደረጉ፡፡

አቶ ታደሰ እየሩስን ወደ ቢሮ ነይ አላት፡፡ እዩ ሳሚ ለዚህ ቤት ምን ማለት እንደሆነ ታውቂያለሽ! ለምንድነው የተቆጣሽው ኸረ ዝም ብዬ ነው የምታውቂው ነገር ካለ ንገሪኝ ቤተሰቦቹ እንዳላዩት ነገሩኝ ችግር እንደደረሰት ግልፅ ነው፡፡ እባክሽ ከዓይንሽ ላይ ያስታውቅብሻል አንድ ነገር እንዳለ ንገሪኝ ፈርተሽ ከሆነ አንቺ መሆንሽን አልናገርም፡፡ እኔ ምንም አላውቅም በቃ ወደ ስራሽ ተመለሺ ሳሮንን ጠራትና ቀስ ብለሽ የት እንደምትሄድ፣ የት እንደምትገባ፣ ተከታተያት፡፡ ጋሼ እዩ ሰሞኑን ለሳሚ ያላት ነገር ትክክል አይደለም ያቺ ለብቻዋ የምትቀመጠው፤ አዎ ሐይማኖት አዎ እሷን ያፈቀረ መስሏት እየዛተች ነበር፡፡ ሳሚ ለእየሩስ ምኗ ነው? ምንም የላቸውም ነበር፡፡ እንዲሁ በድንገት ተነስታ ነው፡፡ በይ ለማንም አታውሪ ዝም ብለሽ ተከታተያት፡፡

ሳሮን ለማረጋገጥ ኢሳቆር ላይ ደወለች፡፡ ሄሎ ኢሳቆር ሳሚ ከትላንት ጀምሮ ጠፍቷል፡፡ ካየኸው ብዬ ነው፡፡ ቤት ደወላችሁ? ደውለናል ትላንት ጠዋት ለስራ እንደወጣ ነው የነገሩን ወይኔ አደረገችው? ምን? መጣሁኝ አለ! እንደደረሰ እዩ ሳሚ የት ነው? አላውቅም! አንድ ነገር ይሁንና አንላቀቅም! አንቺ ጤነኛ አይደለሽም፡፡ ሳሮን ምንድነው? ከእኔ ምንድነው የምትፈልጉት? ከሀገሩ ሁሉ እኔ ነኝ የታየኋችሁ? እየመጣችሁ እዩ ሳሚስ የምትሉኝን ነገር አቁሙ፡፡ ከአጠገቧ ዞር ሲሉ እኔ በቤቴና በልቤ ደብቄ ማኖር ነው የምፈልገው በማያገባቸው ጣልቃ ይገባሉ፡፡

አቶ ታደሰ የሐይማኖትን ስልክ ከሳሚ ተቀብሎ ነበርና ደወለላት ሄሎ ሐይሚ አቶ ታደሰ ነኝ ሳሚ ከትላንት ጀምሮ ከስራም ከቤትም ጠፍቷል፡፡ ምናልባት አይተሽው ከሆነ ልጠይቅሽ ብዬ ነው ፡፡ እኔማ እንዴት አገኘኋለሁ ያቺ ተረገመች እንዳትጎዳው፡፡ ማን ናት? አስተናጋጇ እኔም ጠርጥሬአታለሁኝ ፡፡አንቺ እንዳልገባው ሰው ዝም በይ እሷም ተረጋግታ መስራት ስላልቻለች ----- ይዘ ወጣች ቀጥ ብላ ወደ መዝናኛው ገባች ሳሮን ጠጋ አለቻትና ሳሚ ጠፋ ቤቱ በሀዘን ተሞልቷል ይሄንን የምነግርሽ አንቺንም እንዳትጎዳሽ ነው፡፡

ሐይሚ ብትገለኝ ይሻለኝ ነበር ደስታዬን ከምትነጥቀኝ ከበሩ ልትወጣ ስትል እየሩስ ተከተለቻት ነግሬሽ ነበር የእኔ ነው ብዬ አልሰማ አልሽኝ እኔና እሱ ጣፋጭ ምሽት ነው ያሳለፍነው በጣም ስለደከመው እረፍት አድርግ ብዬው ነው፡፡ ዛሬ ስራ ያልገባው እሷም ሳሚ አልገባም አላስተዋልኩትም ነበር፡፡ ለእናንተ ደስ ብሎኛል በይ ደና ዋይ፡፡ ምን ደስ ይልሻል ተቃጥለሻል ፤ኮንፒሌክሳም ምን ትመስላለች? ሐይሚ ወደ ምትጠላው ወደ ራሷ መዝናኛ ሄደች ሰራተኞቿን ሰብስባ እሷ እየሰደበቻት ፎቶ አንስታት ስለነበር ይህቺ ሴት ታደሰ ግሮሰሪ ነው የምትሰራው የቀን ፈረቃ ናት ስትወጣ ተከታተሏትና ከዚያ ሳትርቁ ደውሉልኝ፡፡

አንተኛው ፖሊስ ጣቢያ ጠይቅ እኔና ሙሉቀን ሆስፒታል እንሄዳለን ፖሊስ ጣቢያ የለም ነበር፡፡ ሆስፒታልም አጡት፡፡ ግራ ገባት! ማልቀስ ጀመረች፡፡ ሙሉ እናንተ ወደ ስራህ በቃ ሂዱ ወደ ስራችሁ ለብቻዋ ከተማውን መዞር ጀመረች፡፡ አጣችው፤ ደከማት፤ ወደ ቤቷ ተመልሳ ማልቅስ ጀመረች፡፡ ድምጿን ከፍ አድርጋ ሳሚ የትነህ? ፈልጌ አጣውህ ፡፡ አምላኬ ምነው ደስታ ሰጥተኸኝ አመስግኜ ሳልጨርስ ነጠከኝ ? አምላኬ እኔ ደስታ አይገባኝም? እባክህ መልስልኝ፤ አትንጠቀኝ ፤ የኔ ፍቅር፣የኔ ሀኪም ህመሜን ፣የልቤን ቁስል እንድታክመኝ እየጠበኩህ ነው ናልኝ ናልኝ የኔ ፍቅር መጥቼ ላድንህ ወይኔ ወዴት ልግባ እያለች ማልቀስ ጀመረች፡፡

ዮሐንስ እየሩስን መከታተል ጀመረ፡፡ ከስራ ስትወጣ ወደ ምግብ ቤት ገብታ ምግብ ጭማቂ ገዝታ ባጃጅ ውስጥ ገብታ መጓዝ ጀመረች፡፡ መሀል መንገድ ስትደርስ ወርዳ በእግሯ መጓዝ ስትቀጥል ዮሐንስ በመኪና ይከተላት ነበር፡፡ ወደ ቤቷ እንደመግባት አስመስላ ታጥፋ መጓዝ ጀመረች፡፡ በፍጥነት ተራምዳ የሆነ መጋዘን ገባች ሳሮንም ትከትላት ስለነበረ በርቀት ቆማ አየቻትና ለአቶ ታደሰ ደወለች፡፡ ዮሐንስም ለሐይሚ ደወለ፡፡ ሐይሚ ሸጉጧን አቀባብላ በመኪና እየበረረች ወደ መጋዘኑ በፍጥነት ደረሰች፡፡ በሩን በእርግጫ ከፍታ የእየሩስ ጭንቅላት ላይ ደቀነችባት፡፡ ሁሉም እንዲንበረከኩ ነገረቻቸው፡፡ በዚሁ አጋጣሚ አቶ ታደሰና ፖሊሶቹ ደረሱ እየሩስንና ግብረ አበሮቿን ወደ እስር ቤት ይዘዋቸው ሄዱ፡፡ ሐይማኖት ድምጿን ከፍ አድርጋ ዮሐንስ አለች፡፡ አጠገቧ የሌለ ይመስል፤ አንፑላንስ ጥሩ፤ ቶሎ በሉ! ሳሚ ሳሚ ንቃ ወይኔ ሞተ መሰለኝ ፍራቻዋ ጨመረ ተንቀጠቀጠች ሳሚ ለሶስት ቀን እና ሌሊት ምግብም ውሃም አልጠጣም ነበር፡፡ አጥቶ ሳይሆን ሐይሚን ከሚያጣ ቢሞት ይሻለው ነበር፡፡ ለዚያ ነበር እራሱን የሳተው፡፡

ሀኪም ቤት ህክምናውን እንዳደረገ ዓይኑን ሲገልጥ ሐይሚን አያት ሐይሚ አለሽልኝ? አንቺን ያጣሁሽ መስሎኝ ነበር፡፡ ተስፋ ቆርጬ መሞት ፈልጌ ነበር፡፡ የኔ ውድ አፈቀርኩሽ ማለት ነው? ያወኩት የታገትኩኝ ጊዜ ነው፡፡ የእኔን ትቼ የማስበው አንቺን ብቻ ነው፡፡ እንዳትጎዳሽ ፈርቼ ነበር ፡፡ አፈቅርሻለሁ! ይሄውልህ አሁን አልሞትኩም ድንጋጤም ፍራቻም በአንተ መገኘት መትረፍ አምልጫለሁ፡፡ ከዚህ በኋላ ለአንዲት ሰከንድ ላጣህ አልፈልግም፡፡ እስማማለሁኝ የኔ ውብ ዓይኖችሽን በደንብ እንዳያቸው ልትፈቅጂልኝ ነው? ኸረ በደንብ አዎ አዎ! በተኛበት ጎተታትና ግንባሯን ሳማት ደግሞ ተመልሰህ ወደ እዚያ ቤት አትሄድም፡፡ ሐይሚ ቤተሰቦቼን የማስተዳድረው እኔ ነኝ አዎ የትናየት ግሮሰሪ አስተዳደር ትሆናለህ፡፡ ደሞ ብዙ ቤቶች አሉ፤ ቤተሰቦችህ እዛ ይገባሉ፡፡ እኔና አንተ አብረን እንሆናለን፡፡ ከጋብቻ በፊት ምንም አናደርግም እሺ! የእኔ የወደፊት ሚስት አፈቅርሻለሁ፡፡

# የድሬዳዋ . . .

ከገጽ 1 የዞረ

ጁሀር እንዳሉት የአገልግሎት ማእከሉ እድሳት ተገልጋዮች በተመቻቸና ሳቢ በሆነ አካባቢ የሚፈልጉትን አገልግሎት በጥራት እንዲያገኙ ታስቦ እንደተገነባ ገልፀው፤ መሰረተ-ልማቱን ከማዘመን ባሻገር አገልግሎቱንም በዛው ደረጃ የማላቅ ስራዎች በቀጣይነት ይሰራሉ ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል አገልግሎት ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ሽፈራው ከሊላ በበኩላቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ ለደንበኞች የሚሰጠውን አገልግሎት ለማሻሻል ሰፊ የሪፎርም ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይም ለደንበኞች አስተማማኝ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት ቀደም ሲል የተገነቡትን የኤሌትሪክ መሰረተ ልማት አቅም የማሳደግ ዘመናዊ የኦፕሬሽን አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ እና ኤሌትሪክ ያልደረሰባቸውን አካባቢዎች ተደራሽ ለማድረግ ሰፊ እቅድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በዚህም በድሬዳዋ አስተዳደር የኤሌትሪክ የመሰረተ ልማት አገልግሎት በአዲስ መልክ በመገንባት አቅሙን የማሳደግ ስራ የተሰራ መሆኑን የገለፁት ኃላፊው የኤሌትሪክ መሰረተ ልማት በማዘመን የኦፕሬሽን አሰራር፣ የስካዳ ሲስተም፣ የደንበኞች አገልግሎት ስራን ሙሉ ለሙሉ ኦን ላይን በማድረግ የኤሌትሪክ አገልግሎት አሰጣጥን ማሳደግ መቻሉን ገልጸዋል፡፡

የድሬዳዋ አስተዳደር ኤሌክትሪክ ሀይል አገልግሎት ሀላፊም አቶ ፍቅረማሪያም አለማየሁ በዚሁ ወቅት እንደተናገሩት የአገልግሎት ማእከሉ ከዚህ በፊት ለደንበኞቹ ምቹ አለመሆኑ እና ሰራተኛውም በተጨናነቀ ክፍል ውስጥ አገልግሎት ይሰጥ እንደነበር አውስተው ማዕከሉን ዘመናዊ እና ምቹ ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጥ ከማቻልም ባለፈ ተጨማሪ አገልግሎቶችን የያዘ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በሰላም ለማ

ፎቶ፡- ሙሉአለም ደሴ

# ህገ - ወጥ . . .

ከገጽ 1 የዞረ

አሰጣጥ ማንዋል ያልቀረፀ መሆኑ አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ውስንነት የፈጠረ መሆኑን በመግለፅ ይህንንም ለመቅረፍ ማንዋል መቅረቡን ተናግረዋል፡፡

አቶ ኤፍሬም አክለውም በከተማችን የተለያየ የኮንስትራክሽን ሳይቶች አካባቢ የሚታየውን ህገ ወጥ የኮንስትራክሽን ግብአት አቀማመጥና የግንባታ የተረፈ ምርት አወጋገድን ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ በተቋሙ ተዘጋጅቶ መቅረቡን ገልፀው፤ መመሪያው ይህንን ችግር ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ ድሬዳዋቸን ንፁህና ውብ እንድትሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ተብሎ እንደሚታመን በመግለፅ በዚህ ደረጃ ችግሩ በሁሉም የአገሪቷ ከተሞች ያለ ቢሆንም ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ አዘጋጅቶ ወደ ትግበራ ለመግባት የተዘጋጀ የመጀመሪያው ባለስልጣን መስሪያ ቤት እንደሚያደርገው ነው ያስታወቁት፡፡

መመመሪያውን ለማዘጋጀት ረዘም ያለ ጊዜ እንደወሰደ የገለፁት ኃላፊው ረቂቅ መመሪያው ለሚመለከተው አካል ተልኮ ማስተካከያ ተደርጎበት ተመልሶ የተላከ ሲሆን በቅርቡ ፀድቆ ወደ ተግባር ይገባል ብለዋል፡፡

በመጨረሻም በተለይ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የቁጥጥር ክፍል ከደንብ ማስከበር ፅ/ቤት ጋር ተቀናጅቶ የጀመረውን የተረፈ ምርት ቁጥጥር አጠናክሮ እንዲቀጥል ያሳሰቡት ኃላፊው መመሪያው ፀድቆ ሲወጣ ደግሞ ይበልጥ ስራውን እንደሚያሳልጠው ገልፀው፤ ሁሉም የተቋሙ ባለሞያዎች ለሠነዶቹ መዳበር በስልጠናው ላይ በንቃት እንዲሳተፉና ለአፈፃፀሙም የድርሻቸውን እንዲወጡ አሳስበዋል፡፡

## በድጋሚ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የንግድ፣ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ በስሩ ለሚገኙ ጽ/ቤቶ ች እና የስራ ሂደቶች የተለያዩ የፅዳት እቃዎች ለመግዛት በዘርፉ የተሰማሩ ህጋዊ ነጋዴዎችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

ስለሆነም በጨረታው ለመወዳደር የሚፈልጉ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ህጋዊ ነጋዴዎች እንዲሳተፉ ይጋብዛል፡፡

1. በዘርፉ ህጋዊ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያለውና የዘመኑን ግብር ከፍሎ የ2016 ዓ.ም የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ማቅረብ የሚችል
2. የግብር ከፋይነትና የቫት ተመዝጋቢነት መለያ ቁጥር ያለው
3. በአቅራቢ ዝርዝር ላይ የተመዘገበ ሆኖ የምስክር ወረቀት ያለው
4. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ቢድ ቦንድ ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ/ በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ወይንም በጥሬ ብር ከመወዳደሪያ ዋጋቸው ጋር አያይዘው አሽገው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. ተጫራቾች የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ) ብር በመክፈል ሰነዱን በመግዛት እና የመጫረቻ ዋጋቸውን በመሙላት ይህ ጨረታ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ተከታታይ ቀናት በድሬዳዋ አስተዳዳር ንግድ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ግዥ ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቢሮ ለጨረታ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
6. ጨረታው በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ላይ ታሽጎ በዚያው ቀን ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎች በተገኙበት 4፡00 ላይ ይከፈታል፡፡ የጨረታ መክፈቻው በእረፍት ቀን ላይ ከዋለ በቀጣዩ ስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ይከፈታል፡፡
7. ተጫራቾች ጨረታውን ማሸነፋቸው ከተገጸላቸውና ውል ከፈጸሙ በኃላ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ህትመቱን አትመው ንግድ፣ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ንብረት ክፍል ገቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
8. ቢሮው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብት አለው፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ**

**0251117680/ 0920459974/ 0915763171**

**የድሬዳዋ አስተዳዳር ንግድ፣ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ**

## የጨረታ ማስታወቂያ

የድሬዳዋ አስተዳደር የቀበሌ 05 ጽ/ቤት በ2016 ዓ/ም በጀት አመት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ግዢዎች ለመፈጸም አቅራቢ ድርጅቶችን በጨረታ እንዲሳተፉ ይፈልጋል፡፡

1. ሎት አንድ አላቂ የጽህፈት መሳሪያዎችን
2. ሎት ሁለት አላቂ የትምህርት ቤት እቃዎች
3. ሎት ሶስት አላቂ የጽዳት እቃዎች
4. የህትመት ስራዎች

ለዚህም፡- 1. የዘመኑ የታደሰ የንግድ ፍቃድ

2. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምስክር ወረቀት

3. የታክስ ከፋይ ምስክር ወረቀት

4. የዘመኑ ግብር የከፈለበት ማረጋገጫ

5. የአቅራቢነት የምስክር ወረቀት

6. ግልጽ ጨረታ ሰነዱን በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት 15 የስራ ቀናት ማለትም ከህዳር 26 /2016 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 16 /2016 ዓ.ም. ድረስ ዘወትር በስራ ሰዓትየጨረታ ሰነዱን ከጽ/ቤቱ ገንዘብ ቤ/ት ቢሮ ቁጥር 105 ቀርበው የማይመለስ 200.00 ብር በመክፈል የጨረታ ሰነዱን መግዛትና መጫረት ይችላሉ፡፡

7. የግልጽ ጨረታ ሰነድ ማስገቢያ ጊዜ ይህ ማስታወቂያ በድሬ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ከህዳር 26 /2016 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 16/2016 ዓ.ም ድረስ ዘወትር በስራ ሰዓት በተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ኦሪጅናል እና ኮፒውን ማስገቢያ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይቻላል፡፡ ጨረታው የሚገባበት ዕለት ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም በዓል ከሆነ በቀጣዩ የስራ ቀናት የጨረታ ሰነዱ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ የሚገባ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

ተጫራቾች የጨረታ ሰነድ ሲያስገቡ የጨረታ ማስከበሪያ በጥሬ ገንዘብ ብር 5000.00 ወይም በባንክ የተመሰከረለት (CPO) ከጨረታው ሰነድ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

8. ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ሰነዱን ለማስገባት ሲመጣ የሚጫረትባቸውን የእቃ አይነቶች ሳምፕል ማቅረብ አለበት

9. ጨረታው የሚከፈተው ታህሳስ 17/2016 ዓም. ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ታሽጎ ከጠዋቱ 5፡00 ሰዓት ላይ ተጫራቶች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ጊዜ በግዢና ፋ/ን/አስ/ዳይሬክቶሬት ቢሮ ይከፈታል፡፡

10. በግልጽ ጨረታ የአሸነፈው ሲለይ የውል ስምምነት እንዲገባ ሲጋበዝ የውል ስምምነት ይገባል፡፡

11. ተጫራቾች በጨረታ ያሸነፈውን እቃዎች በራሱ ትራንስፖርት ት/ቤቱ ድረስ በማምጣት ንብረት ክፍል ገቢ ማድረግ አለባቸው፡

12. ጽ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብት አለው፡፡

**ለበለጠ መረጃ 0251126002/0972262591 በዚህ ስልክ ይደውሉ**

## Invitation to Bid

Place and Date: Dire Dawa, December, 2023

Procurement Reference Number: DDA/LSTDB/002/2016

1. The Dire Dawa Administration Labour, Skills and Technology Development Bureau having legal address at:

| | |
|---|---|
| P.O.Box: | |
| Street Address: | Ali Birra park street |
| Town/City: | Dire Dawa |
| Telephone | |

2. The Dire Dawa Administration Labour, Skills and Technology Development Bureau now invites sealed bids from eligible and qualified bidders for: Construction of Main Hall Maintenance and Renovation, Car Parking Shade and Toilet Work (Location: Ethio-Italy poly-technic college, Dire Dawa).

3. Intended Completion Date for the whole of the Works shall be 150 calendar days.

4. Bidding will be conducted through Local Competitive Bidding procedure contained in public proclamation of FDRE and is open to all Eligible bidders.

5. Interested eligible bidders may obtain further information from Dire Dawa Administration Labour, Skills and Technology Development Bureau and inspect the bidding documents at the address given below from 7:30AM – 12:00 PM & 2:00 – 5:30 PM working hours.

6. Qualifications requirements include: Contractors of category GC/BC-6 & above with license valid for the year 2016E.C. Work Experience is Required

7. A complete set of Bidding Documents in English may be purchased by interested bidders on the submission of a written Application to the address below and upon payment of a non-refundable fee of ETB 500 in Cash.

8. Bidders shall submit their Bids in two envelopes, the first envelop labeled as "Technical Proposal and Bid Security" and the second envelope "Financial Proposal", separate sealed and the two envelopes sealed in on other outer envelope.

9. Evaluation is to be carried out in two stages, Technical Proposal first and Financial Proposal of qualified Bidders next.

10. Bids must be delivered to the address below at or before 3:00 Local Time on 11 Tahisas, 2016E.C. Late bids will be rejected.

11. Bids Will Be Opened In The Presence Of Bidder's Representatives Who Choose To Attend at The Same Date of Submission at 3:30 Local Time.

12. All bids must be accompanied by a Bid Security of ETB 200,000.00 (Two Hundred Thousand Ethiopian Birr only) in the form of Cash, an Unconditional Bank Guarantee, or CPO. The Bid Security shall be valid for 28 days beyond the validity of the Bid.

13. The public body reserves the right to reject any bid and to annul the bidding process and reject all bids at any time prior to contract award, without thereby incurring any liability to Bidders.

14. The address referred to above is:

| | |
|---|---|
| Public Body: | Dire Dawa Administration Labour, Skills and Technology Development Bureau |
| Telephone Number | |
| Street Address: | Ali Birra park street |
| Town/City: | Dire Daw |

## የጨረታ ማስታወቂያ

በድሬዳዋ አስተዳደር የቀበሌ 08 አስ/ጽ/ቤት በ2016 ዓ.ም በጀት ዓመት

ሎት 1. የጽህፈት የቢሮ እቃ ግዢ

ሎት 2. የቢሮ የጽዳት እቃዎች ግዢ

ሎት 3 ከፊል አላቂ የቢሮ እቃዎች ግዢ

አወዳደሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ በዘርፉ የተሰማሩ የሚከተለውን መስፈርት የሚያሟሉ ድርጅቶችን አወዳድሮ ማጫረት ይፈልጋል፡፡

1. በተጠቀሰው የስራ ዘርፍ ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ያለውና የዘመኑን ግብር የከፈለ፡፡
2. በአቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገበና ቫት ተመዝጋቢ የሆነ፡፡
3. ተጫራቾች የጨረታ ማሰከበሪያ ቢድ ቦንድ ለእያንዳንዱ ሎት ብር 5000/ አምስት ሺ ብር/ በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ወይንም ሲፒኦ የመወዳደሪያ ዋጋቸውን አያይዘውና አሽገው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
4. ተጫራቾች ይህ ጨረታ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ተከታታይ ቀናት የጨረታ ሰነዱን በቀበሌ 08 ጽ/ቤት የፋይናንስ ግዢና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 14 በብር 500.00 መግዛት ትችላላችሁ፡፡
5. የጨረታው መክፈቻ ቀን በእረፍት ቀን ወይም በበአላት ቀን ላይ ከዋለ በቀጣዩ የሥራ ቀን ይከፈታል፡፡
6. አሸናፊ ተጫራች ሆኖ የሚገኝ ማሸነፉ በተገለጸለት ቀን ከግዢ አካል ጋር ውል መፈጸም የሚችል እና በውል መፈጸምያ ወቅት 10/100 ውል ማስከበሪያ ማቅረብ የሚችል መሆን ይኖርበታል፡፡
7. ጨረታው በሚከፈትበት ወቅት ህጋዊ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በዕለቱ 3፡00 ሰዓት ተዘግቶ 3፡30 ሰዓት ይከፈታል፡፡
8. ከጨረታ መዝጊያና መክፈቻ ቀንና ሰዓት በኋላ ዘገይቶ የሚመጣ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
9. ቢሮው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ፡-የቀበሌ 08 አስተዳደር ጽ/ቤት የፋይናንስ ግዢና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት**

**በስልክ ቁጥር 0915755100 መነጋገር ይችላሉ፡፡**

## የጨረታ ማስታወቂያ

የድሬዳዋ አስተዳደር ፖሊስ ኮምሽን ለ2016 ዓ.ም በጀት ዓመት በስሩ ለሚገኘው የእግር ኳስ ቡድን እና ብስክሌት ስፖርት ቡድን የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን ግዥ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለማስመዝገብ ይፈልጋል፡፡

ስለዚህ በጨረታ ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች፣

1. የጨረታ ሠነድ የማይመለስ ብር 200/ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል ለ15 ተከታታይ ቀናት በድሬዳዋ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን ፋይናንስና ግዥ ዳይሬክቶሬት የሥራ ሒደት ቢሮ ቁጥር 16 በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡
2. ተጫራቾች የዘመኑ የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር ከፋይ የከፈሉበትን ማስረጃ ማቅረብ ፣ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የአቅራቢነት ምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
3. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና የሚሆንና የጨረታው ውጤት እንደታወቀ የሚመለስ የሚጫረቱበትን እቃ ዋጋ 2% CPO/ወይም በጥሬ ገንዘብ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
4. በተዘጋጀው የጨረታ ሠነድ ላይ ዋጋ ሞልቶ ማቅረብ ተመራጭነት አለው፡፡
5. የዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ ኦርጅናልና ኮፒ በማለት ለየብቻ በማሸግ በአንድ ኤንቨሎፕ ውስጥ በማድረግ በጨረታ ሣጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
6. የጨረታ ሰነድ ህዳር 26 ቀን እስከ ታህሳስ 10 /2016 ዓ.ም. ከ11:00 ሰዓት በድሬዳዋ ፖሊስ ኮሚሽን በፋይናንስና ግዢ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 16 ቀርበው መግዛት ይችላሉ፡፡
7. ጨረታው የሚከፈተው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ታህሳስ 11/2/2016 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3.00 ሣጥኑ ታሽጎ 3.30 ሠዓት ይከፈታል፡፡
8. ፖሊስ ኮሚሽኑ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ ማብራሪያ በስልክ ቁጥር 0251-11-74-55/ 0251-11-37-43 በመደወል መረጃ ማግኘት ይችላሉ። ፖ.ሣ.ቁጥር 1453**

**የድሬዳዋ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን**

## የ ጨ ረ ታማ ስ ታ ወ ቂ ያ

የድሬዳዋ አስተዳደር ቀበሌ 02 1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ2016 ዓ/ም የጽህፈት መሳሪያ፣ የጽዳት እቃ፣ የስፖርት ትጥቅ እና ኤሌክትሪክ እቃ ግዥ በግልጽ ጨረታ በማወዳደር ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም

1. ተወዳዳሪዎች በዘርፉ የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይነት ምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ መሆን አለባቸው፡፡
2. ተጫራቾች ለሚያቀርቡት የጨረታ ዋጋ ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ የጨረታ ማስከበሪያ CPO ከሚያቀርቡት የጨረታ ሰነድ ጋር ማስያዝ አለባቸው፡፡
3. ተጫራቾች የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ የማይመለስ ብር 300/ ሶስት መቶ ብር/ በመክፈል ይህ ማስታወቂያ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከጽ/ቤቱ ቢሮ ቁጥር 15 ቀርበው መግዛት ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ማወዳደሪያ ዋጋቸውን በገዙት የጨረታ ሰነድ ላይ ባለው የዋጋ ማቅረቢያ ቦታ ላይ ሞልተው ኦርጅናል እና ኮፒውን በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
5. ተጫራቾች አንዱን በሌላው ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ አይችሉም፡፡
6. ለት/ቤቶቹ የሚገዟቸውን አገልግሎቶች ብዛት እንደአስፈላጊነቱ መጨመርም ሆነ መቀነስ ይችላሉ፡፡
7. አሸናፊ ድርጅት ከላይ የተገለጹትን አገልግሎቶች የሚሰጡት ለድሬዳዋ አስ/ቀበሌ 02 1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ነው፡፡
8. በጨረታ አሸናፊው የሚሆነው ተጫራች በጨረታ ሰነድ ላይ ለተዘረዘሩት አገልግሎቶች / እቃዎች/ ከእያንዳንዱ አገልግሎት ናሙና /Sample / ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
9. የጨረታው ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን አንስቶ ባሉት ተከታታይ 15 ቀናት ውስጥ ክፍት ሆኖ ከቆየ በኋላ በ16ተኛው ቀን ከጠዋቱ በ3፡00 ሰዓት ተዘግቶ ከጠዋቱ በ3፡30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በቀበሌው ግቢ ይከፈታል፡፡
10. የጨረታው መከፈቻ ቀን የበዓል ቀን ወይም ቅዳሜና እሁድ ላይ ከዋለ በሚቀጥለው የሥራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ላይ ይከፈታል፡፡
11. ተወካዮች የተወከሉበትን ህጋዊ ማስረጃ ይዘው በጨረታው ላይ መካፈል ይችላሉ፡፡
12. ት/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
13. ማንኛውም ተጫራቾች ዋጋውን የጨረታ ሰነድ ላይ ሞልቶ ማህተም አድርጐ መመለስ አለበት፡

**ማሳሰቢያ**

የጨረታ ሰነዱን ለመግዛት ሲመጡ የታደሰ የንግድ ፈቃድ እና የምዝገባ ሰርተፍኬት ኦርጅናልና ፎቶ ኮፒ ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ በሞባይል ቁጥር 0915010461 ወይም በስልክ ቁጥር 0967053085 ደውለው ማብራሪያ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

## በድጋሚ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

በድሬዳዋ አስተዳደር የቀበሌ 01 አስ/ጽ/ቤት የተለያዩ አላቂ የጽሕፈት መሣሪያዎች፣ የጽዳት ዕቃዎች፣ አላቂ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፣ ለመማር ማስተማር የሚረዱ እና የተለያዩ እቃዎችን በጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ የሚከተሉትን መስፈርቶች የምታሟሉ ተጫራቾች መጫረት የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን ፡፡

1. የዘመኑ ግብር የተከፈለበትና የታደሰ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ ማቅረብ የሚችል፡፡
2. የመንግስት ግዥ ላይ እንዲሳተፍ የሚገልጽ ምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል፡፡
3. የተጫራቾች ተጨማሪ የእሴት ታክስ VAT ሰርተፍኬት ማቅረብ የሚችል፡፡
4. ተጫራቾች ጨረታ ማስረከቢያ በባንክ የተረጋገጠ (CPO) 5000 (አምሰት ሺህ ብር) ወይም በጥሬ ገንዘብ ከጨረታ ሰነድ ጋር አያይዞ ማቅረብ የሚችል፡፡
5. ተጫራቾች በእያንዳንዱ ዕቃዎች የሚጫረቱበትን ዋጋ በመግለጽ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ በዚህ በተዘጋጀ ጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል ፡፡
6. ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ድሬዳዋ በሚገኘዉ ቀበሌ 01 አስተዳደር ቢሮ ቁጥር 7 በመምጣት ብር 300 (ሶስት ብር) ከፍለው የጨረታ ሰነዱን መውሰድ ይችላሉ፡፡
7. የጨረታ ማስታወቂያ ሰነዱ ከወጣበት ቀን አንስቶ ባሉት ተከታታይ 15 ቀናት ውስጥ ክፍት ሆኖ ከቆየ በኋላ በ16ኛዉ ቀን ጠዋት 4፡00 ሰዓት ተዘግቶ ከቀኑ 5፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በቀበሌ 01 አስተዳደር ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 7 ይከፈታል ቀኑ የሥራ ቀን ካልሆነ በቀጣይ የሥራ ቀን ይከፈታል፡፡
8. አሸናፊ ተጫራች ያሸነፋቸውን ዕቃዎች በሙሉ በገባዉ ዉል መሠረት ቀበሌ 01 አስ/ጽ/ቤት በመምጣት ንብረት ክፍል ማስረከብ ይኖርበታል፡፡
9. መ/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
10. የሚቀርቡት እቃዎች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆን አለባቸው፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

- ተጫራቾች በጨረታ ሰነድ ላይ ከቀረበው (Specification) ውጪ ሌላ ተመሳሳይ ዓይነት መጨመር የለባቸውም፡፡
- ማንኛውም ተጫራች ዋጋውን በዚህ ዶክመንት ላይ ሞልቶ ማህተም አድርጎ መመለስ አለበት፡፡
- ጨረታ ሰነዱን ለመግዛት ሲመጡ የንግድ ፍቃድና የምዝገባ ሰርተፊኬት ኦርጅናልና ፎቶ ኮፒ ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- የክፍያ ደረሰኞች በየሎቱ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡
- ጨረታው ተከፍቶ ለአሸናፊዎች ከተገለፀ በኋላ የሚያቀርቧቸውንም እቃዎች እያንዳንዱ ለቅድሚያ ሳምፕል ወይም ናሙና ማቅረብ አለባቸው፡፡

**ለበለጠ መረጃ፡- 0920909720 /0915121961 የመስመር ስልክ፡ 0251160386**

**በድሬዳዋ አስተዳደር የቀበሌ 01 አስተዳደር**

## በድጋሚ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የንግድ፣ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ በስሩ ለሚገኙ ጽ/ቤቶች እና የስራ ሂደቶች የተለያዩ ህትመቶችን በዘርፉ የተሰማሩ ህጋዊ ነጋዴዎችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለማሳተም ይፈልጋል፡፡

ስለሆነም በጨረታው ለመወዳደር የሚፈልጉ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ህጋዊ ነጋዴዎች እንዲሳተፉ ይጋብዛል፡፡

1. በዘርፉ ህጋዊ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያለውና የዘመኑን ግብር ከፍሎ የ2016ዓ.ም የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ማቅረብ የሚችል
2. የግብር ከፋይነትና የቫት ተመዝጋቢነት መለያ ቁጥር ያለው
3. በአቅራቢ ዝርዝር ላይ የተመዘገበ ሆኖ የምስክር ወረቀት ያለው
4. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ቢድ ቦንድ ብር 10,000.00 /አስር ሺህ/ በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ወይንም በጥሬ ብር ከመወዳደሪያ ዋጋቸው ጋር አያይዘው አሽገው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. ተጫራቾች የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ) ብር በመክፈል ሰነዱን በመግዛት እና የመጫረቻ ዋጋቸውን በመሙላት ይህ ጨረታ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ተከታታይ ቀናት በድሬዳዋ አስተዳዳር ንግድ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ግዥ ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቢሮ ለዚሁ ጨረታ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
6. ጨረታው በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ላይ ታሽጎ በዚያው ቀን ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎች በተገኙበት 4፡00 ላይ ይከፈታል፡፡ የጨረታ መከፈቻው በእረፍት ቀን ላይ ከዋለ በቀጣዩ ስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ይከፈታል፡፡
7. ተጫራቾች ጨረታውን ማሸነፋቸው ከተገጸላቸውና ውል ከፈጸሙ በኃላ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ህትመቱን አትመው ንግድ፣ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ንብረት ክፍል ገቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
8. ቢሮው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብት አለው፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ**

**0251117680/ 0920459974/ 0915763171**

**የድሬዳዋ አስተዳዳር ንግድ፣ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ**

## ማስታወቂያ

**ለአቶ አብዱልዋሲ መሀመድ**

**ባሉበት**

አመልካች ወ/ሮ ሌይላ መሀመድ በዚህ ፍ/ቤት ቀርበው በእርሶ ላይ እርሶ የሉም በማለት የፍቺ ክስ የተመሰረተቦት ስለሆነ እርሶ አልያም ይህን የፍቺ ክስ አቤቱታ ተቃዋሚ ካለ ለ15/04/2016 ዓ/ም ለሆነ ቀጠሮ እንዲቀርቡ ፤ባይቀርቡ ግን በሌሉበት ፍ/ቤቱ የፍቺ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ያሳውቃል፡፡

**የፌ/መ/ደ/ሸ/ፍ/ቤት**

# የድሬዳዋን ፖሊስ ዘርፈ ብዙ ተግባራት ለመደገፍ ከአምስት ሚሊዮን ብር በላይ የገንዘብ ድጋፍ ተበረከተ

## ❖ ተቋሙን በየትኛውም ሁኔታ ለመደገፍ የግል ባለሀብቶች ቃል ገብተዋል

የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ከለውጡ ወዲህ ያከናወናቸው ጉልህ ተግባራትን ከተለያዩ ተቋማት የመጡ የግል ባለሃብቶች በጎበኙበት ወቅት ተገኝተው ንግገር ያደረጉት የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ክቡር አቶ ከድር ጁሃር እንደገለጹት የድሬዳዋ ፖሊስ ከጊዜ ወደ ጊዜ በአስገራሚ የለውጥ ሂደት ውስጥ መሆኑን ጠቅሰው፤ በቀጣይም የድሬዳዋ ከተማ ሰላም እና ደህንነት አስተማማኝ ለማድረግ የተጠናከረ ስራ እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

ከለውጡ በፊት በድሬዳዋ ከተማ ከባድ የሰላም መደፍረስ እንደነበር ያወሱት ክቡር ከንቲባ አቶ ከድር ጁሃር ከለውጡ በኃላ በተሰሩ ሰፋፊ ስራዎች የከተማው ሰላም እና ደህንነት አስተማማኝ በመሆኑ የግል ባለሃብቶች መዋዕለ ነዋያቸውን ለማፍሰስ ከሚመርጧቸው ከተሞች መካከል የድሬዳዋ ከተማ አንዷ መሆኗን ገልፀው፤ ይሄ ለውጥ የመጣው በአስተዳደሩ አመራር ቁርጠኛ ስራ ፤በድሬዳዋ ፖሊስ አመራር እና አባላት ከፍተኛ ርብርብ እንዲሁም በድሬዳዋ ህብረተሰብ ጥረት መሆኑን ጨምረው ተናግረዋል፡፡

ቀዳሚው ስራችን የዜጎችን ሰላም እና ደህንነት ማረጋገጥ ነው ያሉት የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ ኮሚሽነር ዓለሙ መግራ ሰላም በማስከበር ሂደት የግል ባለሃብቱ ሚና ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዚህ ደረጃ የድሬዳዋ ፖሊስንም



ሆነ የድሬዳዋን ከተማ ለመደገፍ የግል ባለሃብቱ ባሳየው ጥረት መደሰታቸውን ተናግረዋል፡፡

የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ለውጡን ተከትሎ‹‹በ2022 በኢትዮጲያ በላቀ ሞያዊ ብቃት ቀዳሚ የፖሊስ ተቋም ሆኖ ማየት›› የሚል ራዕይ በመሰነቅ የድሬዳዋን ከተማ ሰላም እና ጸጥታ አስተማማኝ ለማድረግ በርካታ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል ያሉት ክቡር ኮሚሽነር ዓለሙ መግራ ይሄንን ራእይ ለማሳካት ይረዳ ዘንድ የተደረገው የገንዘብ ድጋፍ በእጅጉ የሚያግዝ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለተደረገው የገንዘብ ድጋፍ ከልብ እናመሰግናለን ብለዋል፡፡

የጎልድ ውሃ ባለቤት የሆኑት አቶ ብሩክ አዱኛ በበኩላቸው የድሬዳዋ ፖሊስ ከለውጡ ወዲህ ባከናወናቸው የለውጥ ተግባራት መደነቃቸውን ገልጸው፤ ለዚህ ከፍተኛ ጥረት ላለበት ስራ ይበልጥ ሊያግዝ የሚችል የገንዘብ ድጋፍ በማድረጋቸው ኩራት የሚሰማቸው መሆኑን ተናግረዋል፡፡በቀጣይም ከድሬዳዋ ፖሊስ ጎን በመሆን አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ቃል የገቡት አቶ ብሩክ የድሬዳዋ ፖሊስ ላደረገው ደማቅ አቀባበል ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

ባለሀብቶቹ የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያን የጎበኙ ሲሆን ከጉብኝቱ መጠናቀቅ በኃላ የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ለውጡን ተከትሎ ያከናወናቸውን አንጸባራቂ ስራዎችን ለማስቀጠል እንዲቻል የግል ባለሀብት የሆኑት አቶ ብሩክ አዱኛ ሁለት ሚሊዩን ብር ፤ኢ/ር ነገራ ዱጉማ ሁለት ሚሊዮን ብር ኮ/ር መገርሳ ፈይሳ አንድ ሚሊዮን ብር እንዲሁም ኢ/ር ከበደ ለገሰ/የኪ.ቤ.ኪ ባር እና ሬስቶራንት ባለቤት/አንድ መቶ ሺ ብር/ በድምሩ አምስት ሚሊዩን አንድ መቶ ሺ ብር የገንዘብ ድጋፍ ማድረጋቸው ታውቋል፡፡

በዝግጅቱ ማጠናቀቂያ ላይ ለግል ባለሃብቶቹ የምስክር ወረቀት እና ልዩ ሽልማት ከእለቱ ክብር እንግዶች እጅ ተበርክቶላቸዋል ፡፡

# በዜጎች ላይ የሚደርሰውን አስከፊ የትራፊክ አደጋን ለመከላከል የባለድርሻ አካላት ትብብር መጠናከር ወሳኝ እንደሆነ ተገለፀ

የፌደራል መንገድ ደህንነትና መድህን ፈንድ አገልግሎት በድሬዳዋ አስተዳደር አስገዳጅ የ3ተኛ ወገን መድን አዋጅ እና የመንገድ ደህንነት ጉዳዮችን አስመልክቶ ከድሬዳዋ አስተዳደር ፣ ከሱማሌ ክልል ፣ከምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ እንዲሁም ከሐረሪ ክልል የተወጣጡ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ አካሂደዋል ።

በመድረኩ ላይ በመገኘት ንግግር ያደረጉት የፌደራል መንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ጀማል አባሶ እንደተናገሩት አስከፊነቱ ከግዜ ወደ ግዜ እየጨመረ የመጣውን የትራፊክ አደጋን አስቀድሞ ለመከላከል እና ከደረሰ በኃላም የሚሰጠውን ተያያዥ አገልግሎት በተለይ የጤና እና የካሳ ክፍያዎችን በአደጋው ተጎጂ ዜጎች ላይ በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ ዘርፎች የሚያስከትለውን ቀውስ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ማሻሻያዎች ለማድረግ እየሰሩ መሆናቸውን ተናግረዋል ።

አቶ ጀማል አባሶ አክለውም በዜጎች ላይ የሚደርሰው አስከፊ የትራፊክ አደጋን ለመከላከል የባለድርሻ አካላት ትብብር መጠናከር ወሳኝ እንደሆነ



ተናግረው፤ በተለይም በድሬዳዋ አስተዳደር የሚታየው ትብብር እና ቅንጅታዊ አሰራር ወደ ሌሎች ክልሎችም በመውሰድ መተግበር እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል ።

የሚደርሰውን የትራፊክ አደጋን ለመከላከል እንደ ድሬዳዋ አስተዳደር ውጤታማ ስራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን የተናገሩት የድሬዳዋ አስተዳደር ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ ሰአዳ አዋሌ አደጋ ከደረሰ በኃላ የአደጋ ተጎጂ ዜጐችን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ቀውስ ለመቀነስ የወጣውን የተሽከርካሪ አደጋ ሶስተኛ ወገን አዋጅ ተግባራዊ በማድረግ ለዜጎች ነፃ እና አስቸኳይ ህክምና እና የካሳ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ሁላችንም የበኩላችንን የቤት ስራ በአግባቡ ልንወጣ ይገባል ብለዋል።

በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የመንገድ ትራፊክ ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዋ/ኢ/ር ይሄነው ሽፈራው በበኩላቸው በየቀኑ የዜጎችን ህይወት እየቀጠፈ ያለውን የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ በአስተዳደሩ በተከናወኑ ስራዎች አመርቂ ውጤት እየተመዘገበ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህ የተመዘገበው አመርቂ ውጤት ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ላይ በተመሰረተ መልኩ ስራዎች በመከናወናቸው ነው ብለዋል።

የመድረኩ ተሳታፊዎች የተለያዩ ሀሳቦችን በማንሳት ሰፊ ምክክር ያደረጉ ሲሆን ይህንን አስከፊ አደጋ አስቀድሞ ለመከላከል ትኩረት ተደርጎ መሰራት እንዳለበት በመድረኩ የጋራ ሀሳብ ተይዟል ።

በምክክር መድረኩ ላይ ከድሬዳዋ አስተዳደር ፣ ከሱማሌ ክልል ፣ከምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ እንዲሁም ከሀረሪ ክልል የተውጣጡ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል ።

# በማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት አስተባባሪነት የተገነባው የአቅመ ደካማ መኖሪያ ቤት ርክክብ ተደረገ

## ❖ ከ400,00 ሺህ ብር በላይ የሚገመት ገንዘብ ለቤት ግንባታ፣ ለቁሳቁስ እንዲሁም ለአስቤዛ ወጪ ተደርጓል

በምርቃት ኘሮግራሙ ላይ ተገኝተው መልእክት ያስተላለፉት በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የሰው ኃብት አስተዳደር ዘርፍ ኃላፊ ም/ኮሚሽነር ውቢት በፍቃዱ እንደተናገሩት የበጎ ተግባር ስራዎች ስለተረፈን ሳይሆን የምንሰራው ካለን ላይ ቀንሰን የምናደርገው በመሆኑ ይህ የተገነባው የአቅመ ደካማ መኖሪያ ቤት ግንባታ አንዱ ማሳያ መሆኑን ተናግረዋል ።

እንደ ድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ መሪ ቃላችን "በጀግንነት መጠበቅ ፤በሰብአዊነት ማገልገል " ሲሆን በሰላም ወቅት ወደ ማህበረሰብ በመውረድ የተለያዩ ሰብዓዊ ተግባራት ላይ በመሠማራት እንዲሁም ሰላምን እና ፀጥታን በማስጠበቅ ረገድ ፖሊስ ህይወትን በመስጠት እያገለገለ መሆኑን ጠቅሰው፤ የድሬዳዋ ፖሊስ ማህበረሰቡን በማስተባበር የተለያዩ የበጎ አድራጎት ስራዎችን መስራት አጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል ።



ይህን የበጎ አድራጎት ስራ ያከናወኑት አቶ አብዲ ሙክታር ለዚህ የተባረከ ስራ "በመስጠት ውስጥ ያለውን እርካታ ተረድተው "ይህን ስራ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ በገንዘብ ፣ በጉልበት ፤በሃሳብ ላበረከቱት አስተዋፅኦ በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ስም የላቀ ምስጋናቸውን አቅርበዋል ።

ለድሬ ፖሊስ ሚዲያ አስተያየት የሰጡት አቶ አብዲ ሙክታር እንደገለፁት ቤቱን ገንብቶ በማስረከባቸው የተሰማቸውን ደስታ ገልጸው፤ ይህን ስራ ሲሰሩ እና ድጋፍ ሲያደርጉ የመጀመሪያቸው አለመሆኑን ገልፀው፤ በቀጣይ የድሬዳዋ ፖሊስ ከሰላም ማስከበር ባለፈ በፍቅር እያገለገለ በመሆኑ ሊደገፍ እንደሚገባ በመጥቀስ ወደፊትም አብረው ለመስራት ዝግጁ መሆናቸው ተናግረዋል ።

በምርቃት ስነ-ስርዓቱ ላይ የአከባቢው ማህበረሰብ ፣ የወጣት አደረጃጀቶች እንዲሁም የድሬዳዋ ፖሊስ አመራሮች የተገኙ ሲሆን በስተመጨረሻም በበጎ ፈቃድ አገልግሎት የተገነባላቸው ግለሰብ የቁልፍ ርክክብና ድጋፍ ላደረጉ አካላት የምስጋና የምስክር ወረቀት ተበርክቷል፡፡የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ በ2015 ዓ.ም የክረምት የበጎ ፈቃድ ስራዎች ለ31 አቅመ ደካሞች እና አረጋውያን ቤት በማደስ እና አዲስ ቤት ሰርቶ ማስረከቡ ይታወሳል ።

# የአስገዳጅ የ3ኛ ወገን መድህን ሽፋን ያልተገባላቸውን ማንኛውም ተሽከርካሪዎችን ማሽከርከር በወንጀል እንደሚያስጠይቅ የድሬዳዋ ፖሊስ የመንገድ ትራፊክ ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ገለፀ




የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ የጋራ ግብረ ኃይልን በማቋቋም ወደ ቁጥጥር ስራ መግባቱን እና በዚህም የ3ኛ ወገን ሳይገቡ ሲያሽከረክሩ የሚገኙ አሽከርካሪዎች በህግ እንዲጠየቁ የማድረግ ስራ ተጀምሯል ።

ከድሬ ፖሊስ ሚድያ ጋር አጭር ቆይታ ያደረጉት በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የመንገድ ትራፊክ ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዋ/ኢ/ር ይሄነው ሽፈራው እንደተናገሩት በአሁኑ ወቅት በሀገር አቀፍ ደረጃ እጅጉን አሳሳቢ እየሆነ የመጣውን የመንገድ ላይ የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ እንደ አስተዳደር ባለፉት አራት አመታት በተሰሩ ስራዎች ውጤት መመዝገቡ እና በዚህ ረገድ እየተሠጠ የሚገኘው የግንዛቤ ማስጨበጫ፣ የቁጥጥር እና አጥፊዎችን የመቅጣት እና የማስተማር ስራዎችን እየተከናወነ የሚገኝ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከዚህ ባሻገር አደጋዎች በሚከሰቱበት ወቅት በሚደርሰው የትራፊክ አደጋ ተጎጂ የሆኑ ዜጎችን በማንኛውም የጤና የህክምና ተቋማት እስከ ሁለት ሺ ብር የሚደርስ የህክምና አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ በአስገዳጅ 3ኛ ወገን የመድህን ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደንገጉን ገልፀዋል ።

ለዚህ ደንብ ተፈፃሚነት ማንኛውም አሽከርካሪ የ3ኛ ወገን መድህን ሽፋን ሳይገባላቸው ማሽከርከር እንዳይችሉ በወጣው አዋጅ መሠረት ይሄንን ተግባራዊ በማያደርጉ አካላት ላይ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ የጋራ ግብረኃይል በማቋቋም ከህዳር 21ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የቁጥጥር ስራ እያከናወኑ መሆኑን የጠቀሱት ዋ/ኢ/ር ይሔነው ሽፈራው ከአሁን በፊት አስገዳጅ የ3ኛ ወገን ያልተገባላቸው ተሽከርካሪዎች የሚጠየቁት በደንብ መተላለፍ መሆኑን አስታውሰው አሁን ላይ ግን በወንጀል የሚያስጠይቅ ተግባር መሆኑን ጨምረው ገልፀዋል ።

ይህ የቁጥጥር ስራ በቀጣይ በተጠናከረ መልኩ ቀጣይነት ያለው ስራ በማከናወን የትራፊክ አደጋ ከመድረሱ በፊት የመከላከል የመቀነስ እና ተጎጂዎችን ተገቢውን የሆነ የህክምና እርዳታ እንዲያገኙ ታስቦ እየተከናወነ መሆኑን ተናግረዋል ።

የተሽከርካሪ ባለንብረቶችና አሽከርካሪዎች የ3ኛ ወገን የመድህን ሽፋን አለማሳደስ ፣ሳይኖራቸው መንቀሳቀስ በአዋጅ ቁጥር 799/2005 ዓ.ም በተደነገገው መሠረት ከብር 3000 ሺ እስከ 5000 ሺ እንዲሁም ከ1ዓመት እስከ 2 ዓመት በሆነ እስራት እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል ።




19ኛ ዓመት | ቁጥር 854 | ሳምንታዊ ዕትም | ረቡዕ - ህዳር / 26 / 2016 ዓ.ም

# ከ26 ቀናቶች ዕረፍት በኋላ የተመለሰው የኢትዮጲያ ፕሪሚየር ሊግ የመጀመሪያ 6 ተኛ ሳምንት ጨዋታ የሆነው የድሬዳዋ ከተማ እና የወላይታ ዲቻ ጨዋታ በአቻ ውጤት ተጠናቋል።

በብሩክ ደስታ

በ5ተኛ ሳምንት የኢትዮጲያ ፕሪሚየር ሊግ በአዳማ ከተማ ከተሸነፈበት ጨዋታ ኤፍሬም አሻሞና በዳዊት እስጢፋኖስ በመቀየር ወደ ሜዳ መግባት ችለዋል።

በመጀመሪያው አጋማሽ ከፍተኛ የሆነ ፉክክር እና በርካታ ሙከራ ተደርጎበት ነበር።ዕድሎች በመፍጠር ግን የተሻሉ የነበሩት ወላይታ ዲቻዎች ነበሩ። በዚህም ወላይታ ዲቻዎች በ24ተኛው ደቂቃ በጨዋታው ጥሩ እንቅስቃሴ ሲያደርግ የነበረው ቢኒያም ፍቅሬ ግብ በማስቆጠር ወላይታ ዲቻን ቀዳሚ ማድረግ ችሏል። ግብ ካስተናገዱ በኋላ ተነቃቅተው የተሻለ መንቀሳቀስ የቻሉት ድሬዳዋ ከነማዎች በአጋማሹ የመጨረሻ ደቂቃዎች ብልጫ ቢወስዱም ጥራት ያላቸው የግብ ዕድሎችን ግን መፍጠር አልቻሉም።



እንደመጀመሪያው አጋማሽ በሙከራዎች ታጅቦ በቀረበው ሁለተኛ አጋማሽ ሁለት ቅያሪ አድርገው አጋማሹን የጀመሩት ብርቱካናማዎቹ ተሻሽለው መቅረብ ችለዋል።የተሻለ ዕድል የፈጠሩት ድሬዳዋ ከነማዎች በ61ኛው ላይ የከቆመ ኳስ ያገኙት ዕድል ፍሬ አፍርቶ ተቀይሮ የገባው ተመስገን ደረሰ ግብ በማስቆጠር ብርቱካናማዎቹ አቻ ማድረግ ችለዋል።

ከግቡ መቆጠር በኋላ በሁለቱም ቡድኖች በኩል ግብ ለማስቆጠር ጥረት ቢደረግም ተጨማሪ ግብ ሳይስተናገድ ጨዋታው 1-1 በሆነ ውጤት መጠናቀቅ ችሏል።

ከጨዋታው በኋላ አስተያየት የሰጡት የድሬዳዋ ከተማ አሰልጣኝ የሆኑት አስራት አባት "ለጨዋታው ትልቅ ትኩረት ሰጥተውት እንደነበር ገልፀው በሁለተኛ አጋማሽ ያደረጓቸው ለውጦች ቢያንስ አንድ ነጥብ ይዘው እንዲወጡ እንዳስቻላቸው ገልፀዋል። አሰልጣኙ ጨምረውም ሁሉም ቡድን በውድድር ላይ እስካለ ጫና አይቀሬ ነው ካሉ በኋላ የተለየ ጫና ውስጥ እንደሌሉ ገልፀዋል። ድክመቶታቸው ላይ በመስራት ላይ እንዳሉ በመግለፅም ቡድናቸው በቀጣይ እንደሚሻሻል ገልፀዋል"።

## በአይነቱ ለየት ያለ የቦክስ ውድድር በስካይላይት ሆቴል ተካሂዷል።




አዲስ አበባ ከተማ ቦክስ ፌዴሬሽን ከዞላ ዊዝደም ኤቨንት ጋር በመተባበር በአይነቱ ለየት ያለ እና የብሔራዊ ቦክስ ተወዳዳሪዎች የተሳተፉበት የቦክስ ውድድር በስካይላይት ሆቴል ተካሂዷል።

አዲስ ቦክስ ውድድር በሚል ስያሜ በስካይ ላይት ሆቴል በተካሄደው የቦክስ ውድድር በሁለቱም ጾታ ከ54 እስከ 81 ኪሎ ግራም ውድድሮች ተካሂደዋል።

የብሔራዊ ቡድን ተወዳዳሪዎች በተሳተፉበት በዚህ ውድድር የብሔራዊ ቡድን ቡጢኛና የድሬ ቦክስ ቡድን ተወዳዳሪዋ ህገሬ እማኙ ጥሩ ጨዋታ በማሳየት የአዲስ አበባ ተፎካካሪዋን ሮማን አሰፋን ማሸነፍ ችላለች።

ለአንድ ቀን ብቻ በተደረገው ፍልሚያ ላይ ብዛት ያላቸው የቦክስ አፍቃሪዎች የተገኙ ሲሆን የውድድሩ አላማም የቦክስ ስፖርትን ለማነቃቃትና ፕሮጀክቶችን ለማገዝ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

ምንጭ :- ትንግርት ስፖርት

## የድሬዳዋ ከፍተኛ ዲቪዚዮን ውሎ

ከቀናቶች በፊት በደማቅ ስነ ስርአት በይፋ የተጀመረው የድሬዳዋ ከፍተኛ ዲቪዚዮን ሁለተኛ ሳምንት መርሀ ግብሩን ጨርሶ ለ3ተኛ ሳምንት መርሀ ግብር በመንደርደር ላይ ይገኛል።

14 ቡድኖች የሚሳተፉበት የዘንድሮ ከፍተኛ ዲቪዚዮን በበርካታ ታዳሚዎች እንዲሁም ፍፁም ሰላማዊ በሆነ መልኩ ጨዋታዎችም መከናወናቸው ቀጥሏል።

በሳምንቱ የዕረፍት ቀናቶች የ2ተኛ ሳምንት ጨዋታዎች የተደረጉ ሲሆንባቸው በመጀመሪያው ሳምንት የመክፈቻ ጨዋታ በሽንፈት የጀመረው ገንደ አብዲ ቦሩ የአምና የከፍተኛ ዲቪዚዮን አሸናፊ የሆነውን ዋልያን 3-1 በሆነ ውጤት ማሸነፍ ችሏል።

06 ህብረት ሀረር ቡናን 2-1 ሲያሸንፍ መስቀለኛ 01 ቀበሌን እንዲሁም ሳቢያን ህብረት አሸዋን በተመሳሳይ ውጤት 2-0 በሆነ ውጤት ማሸነፍ ችለዋል።

አኳ ድሬ ከድሬ ካባ ጋር 1-1 ሲለያዩ ሆርሞድ ሀፈተ ኢሳን 3-0 በሆነ ውጤት ማሸነፍ ችለዋል።



በከፍተኛ ዲቪዚዮኑ የ2ተኛ ሳምንት የመጨረሻ መርሀ ግብር የሆነው እና በበርካታ ደጋፊዎች ሜዳ በመገኘት የታደሙበት የቀፊራ እና የአዲስ ከተማ ጨዋታ በቀፊራ 2-1 አሸናፊነት ተጠናቋል።

የድሬዳዋ ከፍተኛ ዲቪዚዮን የ3ተኛ ሳምንት ጨዋታዎች በሳምንቱ የዕረፍት ቀናቶች ይከናወናል።